# ፍቅርና ሰላም

በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የጳጳሳት ጉባኤ ጠቅላይ ጽ/ቤት በአማርኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋዎች የሚታተም ወርሃዊ ጋዜጣ

A Monthly Amharic/English Newspaper Published by the Catholic Bishop's Conference of Ethiopa (CBCE)
General Secretariat/ECS

# LINK

ካቶሊካዊ ሲኖዶስ 2014 2016

ለሲኖዶሳዊት ቤተ ክርስቲያን

ቁጥር 569 | መስከረም 2017 ዓ.ም | ዋጋው የኢ.ት. 15.00 ብር




## ብፁዕ አቡነ ደጄኔ (ወልደ ሚካኤል) የሶዶ ሀገረ ስብከት ጳጳስ የእረኝነት አገልግሎታቸውን በይፋ ጀመሩ

" እሱ የሚላችሁን አድርጉ " (የሐ. 2፡-5)

መስከረም 4 ቀን ዕጩ ጳጳስ አባ ደጄኔ በብፁዓን ጳጳሳት ታጀበው ከሲዳማ ክልል ወደ ደቡብ በሚያስገባው የብላቴ ወንዝ ደንበር ጃቶ መንደር ሲደርሱ በስፍራው ይጠብቅ የነበረው የጃቶ ካቶሊክ ቁምስና ምዕመናን የክብር አቀባበል አድርጎላቸዋል።

ገፅ 3



## የነቀምት ሀገረስብከት ተተኪ ጳጳስ ክቡር አቡነ ሚልኪያስ (ጌታሁን ፋንታ) ቅብዓተ ጵጵስና ተከናወነ

"እንደ ፈቃድህ ይሁን" (ማቴ. 6:10)

ለነቀምት ሀገረ ስብከት ጳጳስ እንዲሆኑ በርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ፍራንቺስኮስ ሐምሌ 9 ቀን 2016 ዓ.ም. የተመረጡት የክቡር አባ ጌታሁን ፈንታ የሲመተ ጵጵስና ሥነ ሥርዓት መስከረም 12 ቀን 2016 ዓ.ም. በነቀምቴ ኪዳነ ምሕረት ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ካቴድራል ውስጥ በደማቅ ሁኔታ ተካሂዷል።

ገፅ 3




## መስቀል በዓል በደማቅ መንፈሳዊ ሥነ ሥርዓት ተከበረ

በመላው ሀገራችን በሚገኙ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የመስቀል በዓል በየሰበካው በደመቀ መንፈሳዊ ሥነሥርዓት ተከብሮ አልፏል። በተለይ በዋዜማው ምዕመናና በቁምስናቸው በመገኘት የደመራ የማብራት ሥነ ሥርዓት በፀሎትና በዝማሬ ምሥጋና በማቅረብ በዓሉ ተከብሯል።

ገፅ 4



የብፁዕ ካርዲናል አቡነ ብርሃነየሱስ የ25ተኛ የጵጵስና የብሩራዊ ኢዮቤልዩ ዓመትን በማስመልከት ሥጦታ ለማቅረብ ለሚፈልጉ ሁሉ የቁሳዊ ሥጦታ ቀርቶ የትምህርት ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ወጣቶች እንደሚውል በማሰብ ካርዲናል አቡነ ብርሃነየሱስ የሚል የገንዘብ ድጋፍ ዕድል መመቻቸቱን ገልጸው በተዘጋጀው የባንክ አካውንት መላው ካቶሊካውያን እና በጎ ፍቃድ ያላቸው ሁሉ ለዚህ በጎ አድራጎት ድጋፍ እንዲያደርጉ ጥሪ አቅርበዋል።

**Cardinal Berhaneyesus Fund**

Account Name: **Cardinal Berhaneyesus Fund**
Account Number: **1000523294338**
Commercial Bank of Ethiopia, Mahatema Gandhi Branch
Swift Code: **CBETETAA**

**ፍቅርና ሰላም**

መስከረም 1967 ዓ. ም. ተጀመረ

አሳታሚ ቤተ ሊቀ ጳጳሳት ዘካቶሊካውያን

**በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የጳጳሳት ጉባኤ ጠቅላይ ጽ/ቤት የማኅበራዊ መገናኛና ሕዝብ ግንኙነት ማስተባበሪያ በየወሩ ተዘጋጅቶ የሚወጣ መንፈሳዊ ጋዜጣ**

| | | | |
|---|---|---|---|
| ዋና አዘጋጅ | አባ አበራ ማኬቦ | ፕሩፍ ሪደር | የምሥራች አሰፋ |
| ምክትል ዋና አዘጋጅ | አቤል ሙሴ | ሌይ አውት 1 | ጨረቃ ዘውዴ |
| ማኔጂንግ ኤዲተር | ቤዛዊት አሰፋ | ሌይ አውት 2 | ቤተልሔም ታደሰ |
| ተቀዳሚ ረዳት አዘጋጅና ሪፖርተር/ኤዲተር | ገብሩ ሃ/ዮሐንስ | ስርጭት | ማኅበራዊ መገናኛና ሕዝብ ግንኙነት ማስተባበሪያ |
| ምክትል ረዳት አዘጋጅ | መሳይ ማሪዮ | | |

ፖ. ሣ. ቁ. 2454 አዲስ አበባ ስልክ - (0111) 55 03 00 ፋክስ (0111) 55 31 13 E-Mail - scpr@eccsdco.org Website - https//www.cbce-gs.org

# ርዕሰ አንቀጽ

# ጳጳሳት ያለእኛ እኛ ያለጳጳሳት

**ሁለተኛው የቫቲካን ጉባኤ ሰነዶች ከሰጣቸው ወሳኔዎች አንዱ የጳጳሳት ሃላፊነትና ግዴታ አንዱና ዋናው ነው።**
በክርስትና ጅማሬ ዘለዓለማዊ እረኛ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያኑን ተክሎ አባቱ እሱን እንደ ላከ እርሱም ሐዋርያቶችን ላከ። የእነሱ ተተኪዎች ጳጳሳትም የቤተ ክርስቲያኑ እረኞች እስከ ዓለም መጨረሻ እንዲኖሩ ፈለጋቸው። የፈለጋቸውን አሥራ ሁለቱን መረጠ ከነሱ ጴጥሮስን አለቃ አድርጎ በመሾም እንደ አንድ ማኅበር ሆነው የእግዚአብሔርን መንግሥት በመሰበክ እንዲያስፋፉ ላካቸው (ማቴ 28፡ - 18-20)።

የእነሱ ተልዕኮ በጰንጠቆስጤ ዕለት ፍጻሜውን አገኘ (ሐዋ.ሥራ 2፡- 1-26)። ሐዋርያትም በሁሉ ቦታ ሰብከው መላ ቤተክርስቲያንን ሰበሰቡ። ክርስቶስ ለሐዋርያት በአደራ የሰጣቸው መለኮታዊ ተልዕኮ እስከ ዓለም መጨረሻ የሚኖር ነው። የቤተ ክርስቲያን መቋቋም ለሰው ሁሉ ነውና። ሐዋርያትም የጀመሩትን መለኮታዊ ሥራ በመንፈስ ቅዱስ ረዳትነት የሚቀጥሉ ተከታዮች ጳጳሳትን መርጠው በመሾም መንጋውን እንዲጠብቁ አደራ አሉዋቸው። በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ትጠበቁአት ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ኤጲስ ቆጶስት አድርጎ ለሾመባት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ ( የሐዋ.ሥራ 20/28)።

በቅብዓ ጵጵስና የምስጢረ ክህነት ሙላት ይገኛል፤ ይኸውም የመቀደስ ፣ የማስተማር፣ የማስተዳደር ሥልጣን የሚሰጥ ነው። ይህ አገልግሎት በሥራ የሚውልበትም ከማኅበረ ጳጳሳት አለቃ ከሆኑት ከርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳትና ከአባሎች ጳጳሳት መዓርጋዊ ሱታፌ/ሕብረት/ ሲገኝ ነው። ለጳጳሳት መንፈሳዊ ሥልጣን የሚሰጣቸው በቅብዓተ ጵጵስና ሲሆን ይህ የሚፈፀመው ደግሞ እጆችን በመጫን ነው (1ኛ ጢሞ. 4/14)። ቅዱስ ጴጥሮስና ሌሎችም ሐዋርያት በጌታ ፈቃድ ሐዋርያዊ ማህበር እንደነበሩ እንዲሁም የቅዱስ ጴጥሮስ ተከታይ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳትና የሐዋርያቶች ተከታዮች ጳጳሳት አንድ ማኅበር ናቸው።

አንድ ጳጳስ የጳጳሳት ማኅበር አባል የሚሆነው በምሥጢራዊ ቅብዓት ሲቀባና እንዲሁም ከርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት እና ጳጳሳት ጋር መዓርጋዊ ሲታፌ ሲኖረው ነው። የጳጳሳት ማህበር ከጴጥሮስ ተከታይ ከርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ጋር ካልሆነ ለብቻው ምንም ሥልጣን ሊኖራቸው አይችልም። ምክንያቱም ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት የክርስቶስ ምስለኔ እንደመሆናቸው የመላው ቤተክርስቲያን የጳጳሳትና የምዕመናን አለቃና የበላይ ሥልጣን ያላቸው ናቸው። የጳጳሳት ማኅበር በነገድና በቋንቋ ከተለያዩ ከብዙዎች የተሰበሰቡ ናችው። የእግዚአብሔር ሕዝብም ከሁሉም መሆኑን ያስረዳል። በአንድ አለቃ መሰበሰቡ የመንጋውን አንድነት ያሳያል።

ማኅበረ ጳጳሳት በመላው ቤተክርስቲያን ያለው ሥልጣን የሚሠራበት በጠቅላላ ጉባኤ ነው። ዳሩ ግን በርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ያልተሰበሰበና ያልተቀበለ ጠቅላላ ጉባኤ ሊኖር አይችልም። እያንዳንዱ ጳጳሳ የራሱን ሰበካ ይወክላል ማኅበረ ጳጳሳትም ከርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ጋር መላዋን ቤተክርስቲያን ይ ወ ክ ላ ሉ ። እያንዳንዱ ጳጳስ በተሰጠው ሰበካ ብቻ ባሉት በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ ሥልጣን አለው። ነገር ግን እያንዳንዱ ጳጳስ የማኅበረ ጳጳስት አባል እንደመሆኑ ስለ መላው ቤተክርስቲያን ማሰብ ፣መሥራት ፣መርዳት አለበት ምክንያቱም ወንጌልን መስበክ የማኅበረ ጳጳሳት ግዴታ ነውና።

ጳጳሳት ከርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ሥር ሆነው የሃይማኖት አስተማሪዎች ስለሆኑ ምዕመናን ሁሉ ሊሰሙዋቸው ይገባል። ሃይማኖትንና ሞራልን በሚመለከት ጉዳዮች የእነሱን ምክርና አስተያየት ሊቀበሉ ይገባቸዋል። የምዕመናን መታዘዝ በበለጠ ሊገለጥ የሚገባው ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት በሚያስተምሩትና በሚሰጡት መምሪያ መሆን አለበት። ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት የማኅበረ ጳጳሳት አለቃ በመሆናቸው የምዕመናን ሁሉ የበላይ እረኛና አስተማሪ ናቸው ፤ ስለዚህ ወንድሞቻቸውን በእምነት ለማጥናት ሃይማኖትንና ሞራልን በተመለከተ በሚሰጡት ውሳኔ የማይሳሳቱ ናቸው። ጳጳሳት የተሰጣቸውን የቤተ ክርስቲያን ክፍል የሚያስተዳድሩት የክርስቶስ ምስለኔ በመሆን ነው። ይኸውም በምክር ፣በአብነት፣ በሥልጣንም ሲሰሩበት መንጋውን ወደ ጽድቅና ወደ ቅድስና ለመምራት ብቻ ይሆናል።

ጳጳስ የመንፈሳዊ ቤተሰብ አባት እንደመሆኑ የመልካሙን እረኛ አብነት ተከትሎ ማገልገል ስለ በጎቹም ሕይወቱን መስጠት አለበት። በጸሎት፣ በስብከትና በፍቅር ሥራ በጎቹን ብቻ ሳይሆን ከመንጋው ውጭ ያሉትን ማሰብና መርዳት ይኖርበታል።

ቤተክርስቲያን ከክርስቶስ ከርስቶስም ከአባቱ ጋር አንድ እንደሆነ ለእግዚአብሔር ክብርና ምሥጋን ያበዛ ዘንድ ምዕመናንም ከጳጳሳቸው አንድ ይሁኑ (2ኛ ቆሮ 4;15)። በእግዚአብሔር የተቋቋመው ሐዋርያዊ ተግባር የሚሰራው ልዩ ልዩ ማዕረግ ባላቸው ሰዎች በጳጳሳት፣ በካህናትና በዲያቆናት ነው።

ካህናት አገልግሎታቸውን የሚያከናውኑት የክህነት ሙላት ባላችው በጳጳሳት ሥር ሆነው ነው። ከእነርሱም ጋር በመዓረገ ክህነት ተሳስረዋል። ካህናት ወንጌልን ለመስበክ፣ ምዕመናንን ለመጠበቅ፣ መሥዋዕተ ቅዳሴን ለመቀደስ የተቀቡ ናቸው።

ካህናት የክርስቶስ አካል ፍጻምናውን እንዲያገኝ በጳጳሳቸው ሥልጣን ሥር ሆነው የተሰጣቸውን የጌታ መንጋ ይቀድሳሉ ያስተዳድራሉ። ካህናቶች ጳጳሳቸውን እንደ አባት በፍቅር ይታዘዙታል ፣ ጳጳሱም ካህናቶች ረዳቶቹን እንደ ልጅና ወዳጅ ይጠብቃቸዋል። ካህናቶች በዕለታዊ አካሄዳቸውና በሁሉ ተግባራቸውም ለካቶሊካውያንና ካቶሊክ ላልሆኑ ሃይማኖት ለሌላቸው ሁሉ የቅድስት ክህነታዊ ሕይወትና የጸድቅ ምስክር የመሆን ውዴታዊ ግዴታ ተጥሎባቸዋል።

በማጠቃለያው ጳጳሳት ከእግዚአብሔር እንግዲህ በተሰጣቸው ሥልጣን መሰረት በካህናትና በዲያቆናት እየታገሱ በዘመናት ውስጥ የእግዚአብሔርን መንጋ ይጠብቃሉ ፣ያስተምራሉ፣ ይመራሉ። እኛም ምዕመናን ለቤተ ክህነት ያለንን ክብርና አክብሮት የበለጠ እንድናሳድግ ለጳጳሳት አገልግሎት ይበልጥ የተመቸን እንድንሆን ቸሩ እግዚአብሔር ይርዳን።

**ወስብሐት ለእግዚአብሔር**

## በሰው መሀል ብቸኛ



በዚህ ምድር ላይ ከሚያሳምመው ቃላት አንዱ ብቸኝነት የሚለው ነው። ሁላችንም በአንድም በሌላም ጊዜ ይህንን መራራ ጽዋ ቀምሰነዋል። መዝሙረኛው ዳዊት የብቸኝነትን በረሃና ጽልመት ሲገልፅ “እንደ ሞተ ሰው ከልብ ተረሳሁ እንደ ተበላሸም ዕቃም ሆንኩ” (መዝ. 30፡12) ብሏል። የፈረንሣዩ ንጉሥ ናፖሊዮ “እኔ ባለሚልና ተከታይ እንጂ ጓደኛ ለማፍራት በፍጹም አልፈልግም” ብሎ ነበር። የሚያሳዝነው በሕይወቱ የመጨረሻ ዓመታትን ያሳለፈው አንድ አይዞህ ባይ ሰው ሳይኖረው በብቸኝነት ደሴት ላይ ነበር።

በብቸኝነት ከመሰቃየት በላይ ከባድ ስቃይ የለም ብቸኝነት ከአንድ ሰው ጋር አለመሆን አይደለም። ለአንድ ሰው የመሆን ስሜት እንጂ ዶ/ር ማከስዌል ማልትዝ (Creative living for today) በሚለው መጽሐፋቸው ስለብቸኝነት ሲገልጹ የብቸኝነት ችግር ብቸኛ መሆን (ያለ ሰው) አይደለም። ብቸኛ የመሆን ስሜት እንጂ። ይህን ስሜት ከሰዎች ጋር የሚያቆራርጥና አንዱን ከሌላው የሚለይ ገደል ነው። ብቸኝነት ከስው ጋር እየኖሩ ለራስ ባይተዋር መሆን ነው” ብለዋል። ብቸኞች የሚያገናኝ ድልድይ ከመሥራት ይልቅ የሚለያያ ግንብ ይሠራሉ።

ምንጭ - ስኬታማ የፍቅር ሕይወት (Successful Life of Love) በመምህር ዳንኤል ዓለሙ

ምሥጋና ካነበቡት ላካፈሉን! አቶ ፍቃደ አረዳ ( ወልቂጤ/እምድብር ሀገረስብከት )

## የዕርቀ ሰላም ጸሎት

ፈጣሪ ሆይ የሰላም መሳሪያ እንድንሆን አድርገን። ጥላቻ ባለበት ፍቅር፤ በደል ባለበት ይቅርታ፤ ክርክር ባለበት ስምምነት፤ ጥርጣሬ ባለበት መተማመን፤ ሐዘን ባለበት ደስታ፤ ጨለማ ባለበት ብርሃን፤ እንዲገኝ እናደርግ ዘንድ አብቃን።
ፈጣሪ ሆይ፤ በሕዝባችን መካከል ዕርቅ ይውረድ፤ ሰላምህ ይስፈን፤ አገራችን ኢትዮጵያን ባርክልን ጠብቅልን።
አሜን!

## የሲኖዶሳዊ ጉዞ ጸሎት

*መንፈስ ቅዱስ ሆይ! ና!*

እነሆ በስምህ ተሰብስበን በፊትህ ቆመናል ወደ እኛ ተመልከት፤ እርዳንም። ብቸኛ መሪያችን አንተ ነህ ልቦቻችንን ከፍተህ ማደርያህ አድርግልን። ማድረግ ያለብንን ሁሉ አንተ አስተምረን፣ ሁላችንም በአንድ ላይ መከተል ያለብንን መንገድ አንተ አሳየን። እኛ ደካሞች እና ኃጢአተኞች ነንና፤ ሁከት እንዳናስፋፋ፣ አላዋቂነት ወደ ተሳሳተ ጎዳና እንዳይመራን፣ አድልዎ በድርጊቶቻችን ላይ ተጽዕኖ እንዳያሳድርብን እርዳን። ከእውነት መንገድ እንዳንስት፣ ወደ ዘለዓለማዊ እና ትክክል ወደሆነው ሕይወት አብረን እንጓዝ ዘንድ ከአንተ ብቻ የሆነውን የሕብረት መንፈስን ስጠን።
ይህን ሁሉ በሁሉም ቦታ እና በሁሉም ሰዓት ከአብ እና ከወልድ ጋር አብረህ በሥራ ላይ የምትኖርን አንተን እንለምንሃለን፤ ከዘለዓለም እስከ ዘለዓለም አሜን።

ይህ ዓምድ በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የጳጳሳት ጉባኤ ጠቅላይ ጽ/ቤት የሴቶችና ቤተሰብ ጉዳይ ክፍል ጋር በትብብር የሚዘጋጅ ነው

**“የእግዚአብሔር ማደሪያ ለመሆን እኛን ጻድቃን ያሰኘን ዘንድ ስለ እኛ ኃጢአት ተላልፎ ራሱን ኃጥእ አሰኟልና፤” ብሏል። (2ኛ ቆሮ.5፥21)**

## ብፁዕ አቡነ ደጂኔ ...

ከገፅ 1 የዞረ

በመቀጠልም ጉዞ ቀጥሎ ወላይታ ሶዶ የወላይታ ባህልን የሚገልጽ በአንገት ላይ የሚደረግ ማስታወሻ ሻርፕ አበርክቶላቸዋል። በዚሁ ጊዜ ብፁዓን ጳጳሳትም ለሕዝቡ ቡራኬ ሰጠዋል።

በመቀጠልም ጉዞ ቀጥሎ ወላይታ ሶዶ ከተማ ከመደረሱ አምስት ኪሎ ሜትር ላይ ዕጩ ጳጳስ አባ ደጂኔን ለመቀበል የሶዶ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ቤተሰብ፣ የክልሉ ከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊዎች ተገኝተው አቀባበል አድርገውላቸዋል። ወደ ከተማው እየተቃረቡ ሲመጣ ከባድ ዝናብ የተቀበላቸው ሲሆን ዝናቡ ሳይበግረው በከተማው አደባባይ ላይ ቆሞ የሚጠበቃቸው ከወላይታ ሶዶ ሰበካ የተወጣጡ ወጣት መዘምራን በዝማሬ በሽብሸባ ተቀብለዋቸዋል። የወላይታ ሶዶ ከተማ ማዘጋጃ ቤት የማርሽ ባንድ በስፍራው ተገኝቶ ለዕጩ ጳጳስ አባ ደጂኔ ክብር በማርሽ ሕብረ ድምጽ የተደገፈ ሰላምታ አቅርቦላቸዋል። የማርሽ ባንዱም " ይኸው ለዚህ አብቅቶሀል፣ ከሕዝቡ መሃል ለዚህ አገልግሎት መርጦሃል የሚለውን ዝማሬ በመዘምር እስከ ካቴድራሉ ድረስ ጳጳስትን በማጀብ የከተማውን ሕዝቡ ፍቅር ገልጾላቸዋል። ብፁዓን ጳጳሳት በቅድስት ሥላሴ ካቴድራል በመገኘት ምሥጋና አቅርበዋል።

መስከረም 5/2017 ዓ.ም በሥነ ሥርዓቱ ላይ ከዓዲግራት ሀገረ ስብከት በስተቀር የሁሉም የሀገረ ስብከት ጳጳሳት፣ ሐዋርያዊ አስተዳደሮች፣ የገዳማት ሃላፊዎች፣ ካህናት የተገኙ ሲሆን ፤ ዕጩ ጳጳስ አባ ደጂኔ ልብሰ ተክህኖ በለበሱ ካህናትና ጳጳሳት ታጀበው ሥርዓቱ ወደሚካሄድበት ካቴድራል ሲደርሱ በቦታው ሲጠባበቅ የነበረው ምዕመንና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች በእልልታና በጪብጨባ ተቀብሏቸዋል።

ቅዳሴው ተጀምሮ ወንጌል ከተነበበ በኋላ ሥርዓተ ጳጳስና ከመጀመሩ በፊት ዕጩ ጳጳስ አባ ደጂኔ በገዳማቸው ሃላፊና በሰበካው ካህን ታጀበው መንበረ ታቦት ፊት ሲቀርቡ ብፁዕ ካርዲናል አቡነ ብርሃነየሱስ ሊቀ ጳጳስ ዘካቶሊካውያን ለዚህ አገልግሎት የሚያበቃቸው ከቅድስት መንበር የተላከና የተፈቀደ ደብዳቤ አለ ወይ በማለት ጥያቄ አቅርበዋል። ለዚህ ታላቅ ሃላፊነት ብቁ መሆናቸውን የሚገልጽ ደብዳቤ መኖሩ የቅዱስ ፍራንቼስኮስ ገዳም ሃላፊ አባ ገብረወልድ ገብረጻድቅ የተጻፈ ደብድቤ እንዳለ ገልፀዋል። በዚህ ጊዜ ብፁዕ ካርዲናል እንዲነበብ ጠይቀዋል። ለዚሁ ጉዳይ ሃላፊነት ያላቸው የቅድስት መንበር በኢትዮጵያ ፀሐፊ ብፁዕ ሞንሲኞር ማሲሞ ዕጩ ጳጳስ አባ ደጂኔ በተመለከተ ለእረኝነት የሚያበቃቸውን ከቅድስት መንበር የተላከውን ደብዳቤ በላቲን፣ በእንግሊዘኛ በማንበብ በአማርኛ የተተረጎመውን ጽሁፍ በሕዝበ ክርስቲያኑ ፊት እንዲነበብ አድርገዋል።

በዚህም ደብዳቤ መነሻነት ብፁዕ ካርዲናል ብርሃነየሱስ ሊቀ ጳጳሳት ዘካቶሊካውያንና ጳጳስት ቅድስት መንበር ለዚህ ማዕረግ ብቁ ናቸው ይገባቸዋል ተብሎ የተላከውን ደብዳቤ ከሰሙና የርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ፍራንቼስኮ ማህተም ያረፈበት ጦማር ከተመለከቱ በኋላ ዕጩ ጳጳስ አባ ደጂኔ ለጵጵስና የሚበቃቸውን ሥርዓት ምሥጢር ፈጽመውላቸዋል። ብፁዓን ጳጳሳትም በአዲሱ ጳጳስ ራስ ላይ እጃቸውን በመጫን በተሰጣቸው ፀጋ የመንፈስ ቅዱስ ሃይል ይሞላባቸው ዘንድ ጸልየውላቸዋል።

በመቀጠልም ብፁዕ ካርዲናል በብፁዕ አቡነ ዴጂኔ ራስ ላይ አስኬማ በማድረግ በተጨማሪ በትረ ኖላዊ በመስጠት በቅድስት ሥላሴ ካቴድራል መንበራቸው ላይ እንዲቀመጡና በማድረግ ሙሉ ሀላፊነቱን አስረክበዋቸዋል።

በዚህም በዓል በፁዕ ካርዲናል ብርሃነ የሱስ ለእግዚአብሔር ምሥጋና ያቀረቡ ሲሆን ከዚህ በፊት ሰበካውን ያገለገሉ ከካርዲናል ማሳያ ጀምሮ አባ ፓስካል ፣ አቡነ ዶሞኒኮስ፣ አቡነ ሮደሪጎ ፣አቡነ ፀጋየ ፣ለአስር ወር ሰበካው በተደራቢነት ያገለገሉት አቡነ ስዩም የሆሳዕና ሀገረ ስብከት ጳጳስ አመስግነዋል። ብፁዕነታቸው በመቀጠል የጳጳሳትን የእረኝነት ሃላፊነት በመዘርዘር ቃለ ምዕዳን አሰምተዋል። የጳጳጳስ ሃላፊነት አስመልክቶ የማስተማር፤ የመቀደስ ፤ የማስተዳዳር በዋናነት የጳጳሳት አገልግሎት መሆኑን ገልፀዋል። የጳጳስ ስልጣን እንደ ዓለማው ስልጣን እንዳልሆነ ገልፀው በተለይ ቅዱስ ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ደቀመዝሙሩ የመከረውን ምክር ለጳጳሳት አገልግሎት ታላቅ ሀይል እንደሚሰጥ ገልፀዋል። በተጨማሪ በሰበካው የምታገለግሉ ካህናትም ሆነ ምዕመን ከብፁዕ አቡነ ደጂኔ ጎን በመቆም ቀድሞ የነበራችሁን አገልግሎት አጠንክራችሁ እንደምትቀጥሉ ሙሉ እምነት አለን በማለት ተስፋቸውን ገልፀዋል።

በቅዳሴ ማሳረጊያ ላይ ብፁዕ አብነ ሥዩም የሆሳዕና ሀገረ ስብከት ጳጳስና ጊዜያዊ የወላይታ ሶዶ ሀገረ ስብከት ጳጳስ ከዚህ በፊት ሰበካውን ያገለገሉ ጳጳሳት ሰም በማንሳት ምሥጋና አቅርበዋል። በመቀጠልም ብፁዕ አቡነ ደጂኔ እንኳን ለዚህ ታላቅ አገልግሎት እግዚአብሔር አበቃህ በማለት ወንድማዊ አክብሮታቸውን ገልፀዋል። ወደፊትም ሁለቱ ሰበካዎች ጎረቤት ሰበካ በመሆናችን በጋራ የተጣለብን ሃላፊነት በህብረት እንሰራለን ብለዋል።

- በዚሁ ጊዜ በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ጳጳሳት ጉባኤ ዋና ፀሐፊ አባ ከተማ አስፋው
- በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የቅዱስ ፍራንቼስኮስ ገዳም የበላ ሃላፊ አባ ገብረወልድ ገብረጻድቅ
- በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ካህናት ማህበር ሰበሰሳቢ አባ ፍስሃ ታፈሰ
- የወላይታ ሶዶ ካቶሊክ ሰበካ የምዕመናን ምክር ቤት ተወካይ
- የሶዶ ከተማ ከንቲባና የወላይታ ሶዶ ከተማ ፀጥታ ክፍል ሃላፊዎች
- ከኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን በጋራ የሚሰሩ የምግባረ ሠናይ /ኢጋር/ ደርጅት ተወካይ በየተራ ንግግር አድርገዋል።

በወላይታ ሶዶ ቅድስት ስላሴ ካቴድራልና በተከናወነው በዚህ ሥርዓተ ቅዳሴ መላው በሀገረ ስብከቱ የሚያገለግሉ የሰበካው ካህናትና ገዳማት ፣ ምዕመናን በአካል የተገኙ ሲሆን ሀገረ ስብከታቸውን እንዲመሩ ከተመረጡት አዲሱ ጳጳሳት ጋር በሙሉ ሕብረት ለመሥራት ቃል ገብተዋል። የበዓሉ ሥነ ሥርዓት ረጂም ጊዜ ቢወስድም የበረከትና የፀጋ ዕለት ሆኖ አልፏል።

## የነቀምት ሀገረስብከት ...

ከገፅ 1 የዞረ

ለኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የአዲስ ዓመት በረከት የሆነው የአዲስ ጳጳሳት ቅብዓተ ጵጵስና ከሶዶው ሃገረ ስብከት በመቀጠል በዓመቱ የመጀመሪያ ወር፣ በ12ኛው ቀን የክቡር አባ ጌታሁን ፈንታ በጵጵስና ስማቸው ብፁዕ አቡነ ሚልክያስ ሢመተ ጵጵስና በነቀምት ኪዳነ ምሕረት ካቴድራል ተከናውኗል።

በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የነቀምት ሀገረስብከት ጳጳስ የነበሩት ብፁዕ አቡነ ቫርጌስ ወደ ህንድ ሀገር ከተዘዋወሩበት ጊዜ ጀምሮ ሰበካውን በጊዜያዊ አስተዳዳሪነት ክቡር አባ ግርማ ተስፋዬ ሲመሩ ቆይዋል። ባሰለፍነው ሐምሌ ወር ክቡር አባ ጌታሁን ለነቀምት ሀገረስብከት ቋሚ ጳጳስ ሆነው በርዕሰ ሊቃነጳጳሳት ፍራንቸስኮስ መሾማቸው ይታወቃል። ይህንንም ተከትሎ መስከረም 12 ዕለት በብፁዕ ካርዲናል አቡነ ብርሃነኢየሱስ የአዲስ አበባ ሀገረስብከት ሊቀጳጳስ እና የኢትዮጵያ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ጳጳሳት ጉባኤ ፕሬዝደንት በመሩት መስዋዕተ ቅዳሴ እና የሲመተ ጵጵስና ስርዓት ብፁዕ አቡነ ሚልክያስ የነቀምት ሀገረስብከት ጳጳስ ሆነው ተቀብተዋል። በሥነ ሥርዓቱም የቀድሞ የሀገረ ስብከቱ ጳጳስ ብፁዕ አቡነ ቫርጌስን ጨምሮ ብፁዓን ጳጳሳት፣ የቅድስት መንበር ተወካይ፣ በርካታ ካህናት፣ ገዳማውያን፣ ምዕመናን፣ የሌሎች ሀይማኖት ተወካዮች፣ የመንግስት አካላት እና ጥሪ በዕለቱም ብፁዕ ካርዲናል አቡነ ብርሃነኢየሱስ ባስተላለፉት ቃለምዕዳን ሐዋርያት በኢየሱስ ክርስቶስ በተቀበሉት የመንፈስ ቅዱስ ሀይል አማካይነት ይሰጡት የነበረውን የሚስጥረ ክህነትን ማዕረግ ከትውልድ ወደ ትውልድ የማስተላለፍ አገልግሎት አስታውሰው ይህ የክርስቶስ ቅዱስ ሥራ ህያው ሆኖ በመቀጠል ዛሬም ለኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን አዲስ እረኛ መገኘቱን ገልጸዋል። ብፁዕነታቸው የመልካም ሞኞታቸውን ከገለጹ በኋላ ለብጹዕ አቡነ ሚልክያስ ባስተላለፉት መልዕክት እግዚአብሔር ለሾማቸው አዲስ አገልግሎት በታላቅ ትዕግስት እና በጸሎት እንዲመሩ አደራ በማለት፥ ለመላው ካቶሊካውያንም አዲሱን እረኛ እንዲያግዙ አሳስበው መላው የኢትዮጵያ ጳጳሳትን በመወከል የአብሮነታቸውን መልዕክት አስተላልፈዋል። በመርሃግብሩ ማጠናቀቂያ ብፁዕ አቡነ ሚልኪያስ የምሥጋና መልዕክት ያስተላለፉ ሲሆን፥በመልዕክታቸውም መላው ካቶሊካውያን ለአገልግሎት ቆይታቸው በጸሎት እንዲያግዟቸው ጥሪ አቅርበዋል። የተደረገላቸው እንግዶች ተገኝተዋል።

ብፁዕ አቡነ ሚልኪያስ እ.አ.አ የካቲት 25 ቀን 1973 ዓ.ም. በነቀምት ሀገረስብከት ምዕራብ ወሊጋ አለኩ ቃቄ የተወለዱ ሲሆን በቅዱስ ፍራንቼስኮስ ነገረ መለኮት ትምህርት ቤት የፍልስፍና እና የነገረ መለኮት ማዕከል የክህነት ትምህርት ዝግጅታቸውን በመጨረስ እ.አ.አ ሀምሌ 1 ቀን 2001 ዓ.ም. ክህነት ተቀብተዋል። በአሜሪካ ቺካጎ በሚገኘው የደ ፖል ዩኒቨርስቲ በሰው ሃይል አስተዳደር የማስተርስ ዲግሪያቸውን ተቀብለዋል። ብፁዕ አቡነ ሚልኪያስ በሰኮ የመድኃኔዓለም ቁምስና እና መቲቻ የቅድስት ማርያም ቁምስና ቆሞስ በመሆን ያገለገሉ ሲሆን ለቅዱስ ቪንሰንት ገዳም የሴሚናሪዎች አለቃ፣ በሁለት የኃላፊነት እርከን እና ወቅት የገዳሙ የበላይ አለቃ በመሆን አገልግለዋል። ከዚህም በተጨማሪ በአዲስ አበባ ሃገረ ስብከት 100ኛ ዓመቱን በማክበር ላይ የሚገኘው የላዛሪስት ካቶሊክ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር እና የፍቅር ሥራ ልጆች ማህበር መንፈሳዊ ሃላፊ በመሆን ለጵጵስና እስከተመረጡበት ጊዜ ድረስ አገልግለዋል።

# የኢትዮጵያ ካቶሊካውያን ብሔራዊ ምዕምናን ሐዋርያዊ ተግባር ም/ቤት ለሚቀጥሉት አራት ዓመታት የሚያገለግሉ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት መረጠ

*"አንተ መልካምና ታማንኝ አገሊጋይ በጥቂቱ ታምነህል በብዙ እሾምሀለሁ" (ማቴ 25፡-23)*

ከነሐሴ 23 _ 25 ቀን 20216 ዓ.ም. በሞጆ ቅዱስ ጴጥሮስ ወጳውሎስ ቤተ ክርስቲያን የሱባኤ ማዕከል በተደረገው በዚሁ ጠቅላላ ጉባኤ የሰባት ሀገራት ስብከት የምዕመናን ምክር ቤት የበላይ አገሊጋይ ተወካዮች የተገኙበት ነበር።

በዚሁ ጊዜ የቀድሞ የኢትዮጵያ ካቶሊካውያን ብሔራዊ ምዕምናን ሐዋርያዊ ተግባር ም/ቤት ሰብሳቢ ሻለቃ ፊጣ ቱሉ የኢትዮጵያ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የጳጳሳት ጉባኤ ለምዕመናን መደራጀት ያደረገውንና እየተደረገ ያለውን ሁለንተናዊ ትብብር በመዘርዘር ምስጋና አቅርበዋል። በተመሳሳይ የሰባካ ም/ም/ቤቶች የሥራ አስፈጻሚ አባላት ለእምነታቸው ያላቸውን ቅንነት በመግለጽ ደከመኝ ሳይሉ ጊዜያቸውን ሰጠው ለአገልግሎት የሚያሳዩት ቀና መንፈስና ሁለንተናው ትብብር ምስጋና አቅርበዋለ። ይህ ቀና አገልግሎት ተጠናክሮ የመቀጠል ሃላፊነት የሁላችን ነው ብለዋል።

ሕገ ደንቡ በሚፈቅደው መሰረት በሀገራቸን በነበረው የተለያዩ ተገዳሮቶች እና የሁኔታዎች በብሔራዊ ደረጃ ምርጫ ባይደረገም ምዕመናን እምነታቸውን ተገንዝበው መብትና ግዴታ ተረድተው እንዲፈጽሙ የተቻለው ሁሉ መደረጉን ገልጸዋል።

በዚሁ ስብስባ የኢትዮጵያ ካቶሊካውያን ብሔራዊ ምዕምናን ሐዋርያዊ ተግባር ም/ቤት የሚያገለግሉ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት መተካት አንዱ አጀንዳ ሲሆን ጉባኤው ተነጋግሮበት አስፈላጊነቱን አምኖበት ምርጫው እንዲደረግ የተወሰነበት ነበር። በዚህ አጀንዳ በክቡር አባ አበራ ማኬቦ የኢትዮጵያ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የጳጳሳት ጉባኤ ጽ/ቤት የሐዋርያዊ ኮሚሽን ሃላፊ የሚመራ የምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴ ተሰይሞ ተተኪ የሥራ አስፈጻሚ አባላት ተመርጠዋል።

- አቶ ማርቆስ ዮሐንስ / ሰብሳቢ/ አዲስ አበባ ሀ/ስብከት
- አቶ ታከለ ጴጥሮስ /ም/ሰብሳቢ/ መቂ ሀ/ስብከት
- አቶ ፍቅሬ ፈርሻ / አባል/ እምድብር ሀ/ስብከት
- አቶ መስፍን መሮ / አባል/ ጂማ ቦንጋ ሀ/ስብከት
- አቶ በቀለ ሞሊሶ / አባል/ ወላይታ ሶዶ ሀ/ስብከት
- አቶ ጌታቸው ሄራሞ / አባል/ ሆሳዕና ሀ/ስብከት
- ወ/ት ሳራ አዴቦ / አባል/ ሆሳዕና ሀ/ስብከት ተመርጠዋል።



ይህ ዓምድ በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያንን የጳጳሳት ጉባኤ ጠቅላይ ጽ/ቤት ከሶሻል ሪሃብሊቴሽን ክፍል ጋር በትብብር የሚዘጋጅ ነው

**"ነገር ግን የባርያን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ፥ በምስሉም እንደ ሰው ተገኝቶ ራሱን አዋረደ፥ ይኸውም ለመስቀል ሞት እንኳ የታዘዘ ሆነ፤" ብሏል። (ፊል.2፥7-8)**

**መስቀል በዓል ...**

ከገፅ 1 የዞረ

በአዲስ አበባ ጳዮን ማርያም ቁምስና በዓሉ እጅግ በደመቀና በአማረ ዝግጅት ተከብሮ ውሏል። ቁምስናው በዓሉን ለማክክበር ቅድመ ዝግጅት በማድረግ በአዲስ አበባ ለሚገኙት ቁምስናዎች ጥሪ ያደረገ ሲሆን ጥሪውን በመሰማት ምዕመናን ያሰባሰበ በዓል ነበር። በዚሁ ጊዜ በክቡር አባ ተስፋዬ ወልደማርያም በአዲስ አበባ ሰበካ የብፁዕ ካርዲናል አቡነ ብርሃነኢየሱስ ሊቀ ጳጳሳት ዘካቶሊካውያን እንደራሴ በዓሉን አስመልክቶ ያስተላለፉትን ቃለ ምዕዳን ይዘን ቀርበናል።

*በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን።*

የዘመናት ባለቤት የሆነው መድኃኔዓለም ክርስቶስ እንኳን ከዘመነ ዮሐንስ ወደ ዘመነ ማቴዎስ በሰላምና በጤና አሸጋገረን። ዓመቱ የሰላም፣ የፍቅር፣ የዕርቅ፣ የደኅንነት የመተሳሰብ የበረከት ዓመት ያድርግልን። የመስከረም ወር በአገራችን ኢትዮጵያ ልዩ ትርጉም ያለው ወር ነው። ወሩን ከሌሎች ወራት ልዩ የሚያደርገው ይህ ወር የአዲስ ዓመት መጀመሪያ ሰማይ በከዋክብት ምድር በአበባ አሸብርቀው የሚታዩበት ጊዜ በመሆኑ የአበባና የቅዱስ መስቀል በዓል ማክበሪያ የሆነ ልዩ ወር መሆኑ ነው።

ይህ መስቀል ጌታችን መድኃኒታች ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለበት እውተኛ የመስቀል በዓል ነው። ብዙ ተአምራት ታይቶበታል ፣ ሕሙማንም ተፈውሰውበታል። ያገኘችው ቅድስት እሌኒ የንጉሥ ቈስጢንጢኖስ እናት መሆንዋን በታሪክ ተመዝገቦ ይገኛል። "መስቀል ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሞቱ ሞትንና የሞትን ኃይል ድል ያደረገበት ኃጢአትንና የኃጥአን ከተማ ከጨለማ ወደ ብርሃን ያወጣበት፣ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ዕርቅ የተደረገበት የሠላምና የፍቅር ዜና የታወጀበት የሠላም ዙፋናችን፣ የነጻነትና የድል ምልክት አርማችን ነው።

እግዚአብሔር እጅግ ስለወደደን በልጁ መስቀል ለኛ ያለውን ፍቅር ገለጸልን (ዮሐ. 3፡16) ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አካሉ ለዓለም ቤዛ በመስቀል ተሰቅሎ ሥጋውን ቆርሶ ደሙን አፍስሶ፣ የሰውን ዘር ከወደቀበት አንሥቶ፣ ወደ ቀድሞ ክብሩ መልሶ ነጻነቱን ያወጀበት በሰው ልጅ ኃጢአት ምክንያት የተዘጋውን የገነት በር የተከፈተበት በሰማያውያንና በምድራውያን መካከል አንድነት የመሠረተበት የማዳን ሥራ ያከናወነበት ስለሆነ መስቀል ኃይላችን፣ አርማችንና መመኪያ ጋሻችን ነው። "እኔም ከምድር ከፍ ብዬ በተሰቀልሁ ጊዜ ሰውን ሁሉ ወደኔ እስባሁ" (ዮሐ. 12፡31)። ብሎ እንዳስተማረን ሁሉን ወደራሱ ያቀረበበት፣ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የነበረውን የጥል ግድግዳ ያፈረሰበት፣ የሰው ዘር ሁሉ አንድ ያደረገበት፣ የኃጢአት ዕዳችንን የደመሰሰበት፣ መከፋፈልንና መለያየትን አስወግዶ ሰላም የሰጠበት ስለሆነ መስቀል የአዲስ ኪዳን መሠረት ነው።፡ "መስቀል ብርሃን ለኵሉ ዓለም መሠረተ ቤተክርስቲያን ወሃቤ ሰላም" ማህሌተ ቅዱስ ያሬድ።

ፍቅር በተግባር ሲገለጽ ሰላምን ይወልዳል፣ ሰላም ሲሰፍን ልማትን፣ አንድነትን፣ ብልጽግና ያስፋፋል። ፍቅር ባለበት ሰላም ሰላም ባለበት ፍቅር አለና መስቀል ከምድራዊ ጠላትና ከአጋንንት ጥቃት የምንከላከልበት መሣሪያችን ነው።

በፊተኛ ክፍለ ዘመን የነበረ የክርስቲያኖች ወዳጅ ንገሥ ቈስጢንጢኖስ "በዚህ የመስቀል ምልክት ጠላትህን ድል ትነሣለህ" የሚል ጽሑፍ በሰማይ በማየቱ በሠራዊቱ ልብስ፣ በጦሩ መሣሪያ በፈረሱ ኮርቻ ሁሉ የመስቀል አርማ አሠረቶ ወደ ጦርነቱ በገባ ጊዜ ጦርነቱን በቀላሉ ድል ለማድረግ ችሏል። እኛም ከሥጋዊና ከመንፈሳዊ ጠላት ራሳችንን ለመጠበቅ በመስቀል ምልክት ፊታችንን እናማትባን። መስቀልንም እንሰራለን። "ለሚፈሩት ምልክት ሰጠሃቸው ከቀስት በፊት ያመልጡ ዘንድ ..."መመሪያችን ነው (መዝ. 60፡4)።

**ትእምርተ መስቀል /ማማትብ/**

የክርስቶስ መስቀል የምናከብርበት በቀላሉና ግልጹ መንገድ ትእምርተ መስቀል በመሥራት /በማማተብ/ ነው። የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች የመስቀል ምልክት የሚያደርጉት ግንባራቸው ላይ ነበር። ቀስ በቀስ በትልቅ ምልክት ተተካ ። ይሄውም ግንባር ላይ ብቻ ተወስኖ የነበረው ከግንባር ወደ ደረት ከዚያም ወደ ግራ ትከሻ ወደ ቀኝ ትክሻ ማድረግ ተጀመረ።

የመስቀል ምልክት ማድረግ ወይም ማማተብ ልክ ጋሻን ይዞ "ከክርስቶስ ፍቅር ማን ይለየኛል (ሮሜ 8፡35) እንደማለት ነው። ጌታችን መድኃኒታች ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ በተሰቀለበት ወቅት መስቀል ኢየሱስን ተሸከመው እንጂ ኢየሱስ መስቀሉን አልተሸከመውም ስለዚህ እኛም በመስቀሉ የድጋፍ መሠረት እናገኛለን።

ትምህርተ መስቀል ማድረግ ተጨባጭ የሆነ የእምነታችን ይዘት ነው። ከላይ ከግንባራችን እንጀምራለን። ይህ የሚያሳየው ሁሉም ነገር የሚጀምረው ከላይ ከሰማይ የሁሉም ነገር የመጀመሪያ ፈጣሪ የሕይወት ምንጭ ከሆነው ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደ ሆነ ነው። ከዚያም እጃችን ወደ ደረታችን እናወርደዋለን። ይህም የሚያሳየው እግዚአብሔር ከሰማይ ወርዶ በልባችን በሚኖረው ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው እንደሆነ ነው። ይህ ከላይ ቀጥታ የሚወርደው መስመር ምስጢረ ሥጋዌን ያሳናል። ይህን መስመር በመከተል ከግራ ወደ ትከሻችን ወደ ቀኝ ትከሻችን መስመር እናሰምራለን። ይህ ደግሞ የሚያሳየው ሁሉንም ነገር ያገኘነው አንድ ያደረገው መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ ነው። እግዚአብሔር በዚህ ዓለም ላይና ወደ ጎን ባለን ትስስርና ግንኙነት ውስጥ የሚሰራው በመንፈስ አማካይነት ነው።

ትመህርተ መስቀል ከማድረግ ፊንታ እኛ እራሳችን እጆቻችንን በመዘርጋት መስቀል ልንሆን እንችላለ። የሰው ልጅ እጆቹ ሲዘረጉ በጣም ውብ ነው። ይኸውም ወደ እግዚአብሔር ለመፀለይ አሊያም ጎረቤቱን ለማቀፍ ነውና። የመስቀል ምልክት በቋሚነት የሚያስታውሰን ክርስቶስ ጋር እንደተሰቀልን እኛ የራሳችንን ሕይወት እንደማንኖር ነው።/ ገላ 2፡19/

መልካም የመስቀል በዓል

# ርዕሠ ሊቃነ ጳጳሳት ፍራንቼስኮስ ከሰኞ ነሐሴ 27 ቀን 2016 እስከ መስከረም 3 ቀን 2017 ዓ. ም. በእስያ እና በኦሼኒያ 45ኛው ሐዋርያዊ ጉብኝታቸውን ጨርሰው ወደ ቅድስት መንበር ተመለሱ



ርዕሠ ሊቃነ ጳጳሳት ፍራንቼስኮስ በጵጵስና ዘመናቸው ረጅም የሆነውን የአሥራ ሁለት ቀን ሐዋርያዊ ጉብኝት በኢንዶኔዢያ፣ በፓፑዋ ኒው ጊኒ፣ በቲሞር ሌስቴ እና በሲንጋፖር አድርገዋል። በጉብኝታቸው የሰላም እና አንድነት፣ የምክክር እና የሐይማኖት ህብረት እንዲበረታታ የሚያግዙ መድረኮች ላይ በመሳተፍ አባታዊ መልዕክቶቻቸውን እና ቡራኬያቸውን ለሀገራት መሪዎች፣ ለገዳማውያን እና የሐይማኖት አባቶች፣ለወጣቶች፣ ለመላው ካቶሊካውያን እና የሀገራቱ ዜጎች አስተላልፈዋል።

ርዕሠ ሊቃነ ጳጳሳት ፍራንቼስኮስ በኢንዶኔዥያ በነበራቸው ቆይታ በጃካርታ ኢስቲቅላል መስጊድ የተካሄደውን የሃይማኖቶች ስብሰባ ጨምሮ በርካታ ጉብኝት አድርገዋል። ቅዱስነታቸው ከታላቁ ኢማም ዶ/ር ናሳሩዲን ኡመር ጋር በመሆን በልዩነት መካከል አንድነትን የመንከባከብን አስፈላጊነት ላይ ተወያይተዋል። "የወዳጅነት ድልድይ" በመባል የሚታወቀውን የእመቤታችን ፍልሰተ ማርያም ቤተክርስቲያንን ከኢስቲቅላል መስጊድ የሚያገናኘው ከመሬት በታች የተገነባውን ድልድይ ለሰው ልጅ ህብረት ታላቅ ምሳሌ መሆኑን ገልጸዋል። ከወጣቶች ጋር ባደረጉት ቆይታም ልዩነቶች ከግጭት ይልቅ ወደ ውይይት እንደሚያመሩ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፤ ይህም መግባባትና መስማማትን ያጠናክራልም ብለዋል። በጉብኝታቸው ማጠቃለያም በሺዎች የሚቆጠሩ ካቶሊካውያን በተገኙበት መስዋዕተ ቅዳሴ ያሳረጉ ሲሆን ምእመናን ወንድማማችነትን እና በማህበረሰባቸው ውስጥ ደግነትን እንዲያሳድጉ አበረታተዋል።

ሐዋርያዊ ጉዟቸውን በመቀጠል ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ፍራንቼስኮስ ወደ ፓፑዋ ኒው ጊኒ በማምራት የሀገሪቱን የባህል እና የጎሳ ስብጥር አድንቀው፣ ብጥብጥ እና መከፋፈል እንዲቆም ተማጽነዋል። የሀገሪቱን ባለስልጣናትን ባነጋገሩበት ወቅት የጤና፣ የትምህርት እና የሥራ እድሎችን ለማሻሻል ውይይት እና ትብብር እንደሚያስፈልግ አሳስበዋል። ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ወደ ፖርት ሞሬስቢ ባደረጉት ጉብኝት ከጎዳና ተዳዳሪዎች እና አካል ጉዳተኞች ጋር ተገናኝተው አባታዊ ቡራኬ ሰጥተው በእግዚአብሔር ፊት ያላቸውን የተፈጥሮ ዋጋ አስታውሰዋል። በተጨማሪም የአካባቢው የካቶሊክ ቤተክርስቲያን ገዳማውያን ፈተናዎች ቢኖሩባቸውም በተስፋና በድፍረት ተልእኳቸውን እንዲቀጥሉ አበረታተዋል።

ሶስተኛዋ የሐዋርያዊ ጉብኝታቸው መገኛ በሆነችው ቲሞር ሌስቴ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ፍራንቼስኮስ በታላቅ የአቀባበል ስሜት ከተሰበሰቡ ሰዎች ጋር ተገናኝተዋል። በተለያዩ መድረኮች ባስተላለፏቸው መልዕክቶች የሀገሪቷን ንቃትና ወጣትነት አንስተው ህጻናትን መቀበል እና መንከባከብ የሀገሪቱ የወደፊት እጣ ፈንታ ምልክት መሆኑን አስገንዝበዋል። ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ፍራንቼስኮስ በቲሞር ሌስቴ ከአገሪቱ አጋማሽ ከሚሆን ህዝብ ጋር ከ600ሺ በላይ ካቶሊካውያን በተገኙበት መስዋዕተ ቅዳሴ ያሳረጉ ሲሆን በስብከታቸውም ለወጣቱ ትውልድ ቦታ እንዲሰጡ እና ለደህንነታቸው ቅድሚያ እንዲሰጡ በማበረታታት ለቲሞር ሌስቴ ሰዎች እምነት እና ጽናት ያላቸውን ጥልቅ አድናቆት አንጸባርቀዋል።

የሐዋርያዊ ጉዟቸው መጨረሻውን ያደረገው ሲንጋፖር ሲሆን ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ፍራንቼስኮስ ሞቅ ያለ አቀባበል ተደርጎላቸዋል። ቅዱስነታቸው ሲንጋፖርን እንደ የእድገት፣ የአብሮነት እና የአካባቢ ጥበቃ ተምሳሌት አድርገው እውቅና ሰጥተዋታል። ከሀገሪቱ ባለስልጣናት ጋር በነበራቸው ቆይታም በማህበራዊ ፍትህ እና ዘላቂነት ላይ ቀጣይነት ያለው ጥረት እንዲደረግ ጥሪ አቅርበዋል። ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት በሲንጋፖር ቆይታቸው ከሃይማኖት መሪዎችና ወጣቶች ጋር በመገናኘት በተለያዩ ሃይማኖቶች መካከል ያለውን አንድነትና ውይይት አስፈላጊነት አጽንኦት ሰጥተዋል። ሁሉም ሀይማኖቶች ወደ እግዚአብሔር የሚያስኬዱ መንገዶች መሆናቸውን በመግለጽ ወጣቶች በማህበረሰባቸው ውስጥ መግባባትን እና አንድነትን እንዲያሳድጉ ሐዋርያዊ መልዕክት አስተላልፈዋል። ርዕሠ ሊቃነ ጳጳሳት ፍራንቼስኮስ በሲንጋፖር ብሔራዊ ስታዲየም ባደረጉት ቅዳሴ ሐዋርያዊ ጉዟቸውን ያጠናቀቁ ሲሆን ስብከታቸውም የቅዱስ ወንጌል አንኳር በሆነው ፍቅር ላይ ያተኮረ ነበር።

መስከረም 3 ቀን 2017 ዓ.ም. ወደመንበራቸው የተመለሱ ሲሆን 45ኛው የርዕሠ ሊቃነ ጳጳሳት ፍራንችስኮስ የሐዋርያዊ ጉብኝት የቅዱስነታቸውን የሰላም፣ የውይይት እና ፍጥረታትን የመንከባከብ ተልእኮ በጉዟቸው ሁሉ የታየበት ሆኖ አልፏል። ወደ ሮም ሲመለሱም በዚህ ታሪካዊ ጉብኝት ወቅት እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ስላደረገችላቸው ጥበቃ ምሥጋና ለማቅረብ በሮም በሚገኘው የቅድስት ድንግል ማርያም ታላቁ ባዚሊካ በማሳረጊያ ጸሎት አጠናቀዋል።

ይህ ዓምድ በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያንን የጳጳሳት ጉባኤ ጠቅላይ ጽ/ቤት ከትምህርት ክፍል ጋር በትብብር የሚዘጋጅ ነው

**"ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ ሁሉ በክርስቶስ ደግሞ ሕያዋን ይሆናሉና፤" የተባለው። (1ኛ ቆሮ.15፥22)**

VATICAN MEDIA

# የቫቲካን ሚዲያ ገጽ

# በዕድገት ሂደት አብሮ መጓዝ

## ክፍል 2

የራስን ማንነት በመደበቅ፣ በአንጻሩ በእፍረተ ቢስነት የሌሎች ሰዎችን ዝርዝር ሕይወት በማወቅ አስከፊ ጉጉት በተጠመደ ባህል ውስጥ፣ ቤተክርስቲያን አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ሁሉ ሌሎችን በቅርበትና በአዘኔታ መመልከት ይኖርባታል። በዓለማችን፣ ካህናትና ሌሎች ሐዋርያዊ ሠራተኞች የክርስቶስን የቅርበት መዓዛና የእርሱን ግላዊ አመለካከት ማሳየት ይችላሉ። ቤተክርስቲያን፣ ካህናት፣ ደናግልና ምእመናንን በሌላው የተቀደሰ መሬት ፊት ያለውን ጫማችንን እንድናወልቅ (ንጽ.ዘጸ.3፡5) ከሚያስተምረን ከዚህ ‹‹አብሮ የመጓዝ ጥበብ›› ጋር ማስተዋወቅ አለባት። የዚህ የአብሮነት ጉዞ እርምጃ የማያቋርጥና ተስፋ የሚሰጥ፣ የሚያድን፣ ነጻ የሚያወጣና በክርስቲያናዊ ሕይወት ማደግን የሚያበረታታ እንዲሁም ቅርበታችንንና አዘኔታችንን የሚያንፀባርቅ መሆን ይገባዋል።

የጋራ መንፈሳዊ ጉዞ የሌሎች ሰዎችን እውነተኛ ነጻነት ወደምናገኝበት ወደ እግዚአብሔር ሊያቀርብ ይገባል። አንዳንድ ሰዎች እግዚብሔርን በመተው ነጻ እንሆናለን ብለው ያስባሉ፤ በተፈጥሮአቸው ወላጅ የሌላቸው፣ ረዳት አልባና ቤት አልባ መሆናቸውን ማየት ይሳናቸዋል። መንፈሳዊ ተጓዦች መሆናቸው ቀርቶ ራሳቸውን እየቀያየሩ ከቶ የትም ቦታ የማይደርሱ ዓላማ ቢሶች ይሆናሉ። ከእነርሱ ጋር አብሮ መጓዝ በራሳቸው መጠመድን የሚደግፍ የሕክምና ዓይነት ከሆነና ከክርስቶስ ጋር ወደ አብ የሚደረግ ጉዞ መሆኑ ከቀረ ውጤት አልባ ይሆናል።

ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ ዛሬ፣ ከሌሎች ጋር አብሮ ከመጓዝ ልምዳቸው ተነሥተው በጎችን መንጋውን ከሚበትኑ ተኩላዎች ለመጠበቅ ይችሉ ዘንድ ማስተዋልን፣ ብልህነትን፣ ትዕግሥትንና ታዛዥነትን በሚገባ የሚያውቁ ወንዶችና ሴቶች ያስፈልጉናል። እኛም ከመስማት የሚበልጠውን የማዳመጥን ጥበብ መለማመድ ያስፈልገናል። በግንኙነት ውስጥ ማዳመጥ እውነተኛ መንፈሳዊ ግንኙነት እንዲኖር ለሚያደርግ ቅርበት ልብን ዝግጁ ማድረግ ነው። ማዳመጥ ይረዳል። ወደ እውነተኛ የዕድገት መንገድ ለመግባትና ለክርስቲያናዊ አስተሳሰብ ያለንን ጉጉት ለመቀስቀስ የምንችለው በአክብሮትና በአዘኔታ በማዳመጥ ብቻ ነው። ይህ ጉጉት ለእግዚአብሔር ፍቅር ሙሉ ምላሽ ለመስጠትና እርሱ በሕይወታችን ውስጥ የዘራው ነገር ፍሬ እንዲያፈራ የሚያስችለን ነው። ነገር ግን፣ ይህ ሁል ጊዜ ትዕግሥትን ይጠይቃል፤ ቅዱስ ቶማስ አኳይናስ እንደሚነግረን፣ ማንኛውም ሰው ጸጋና ፍቅር ሊኖረው ይችላል፣ ሆኖም በማያቋርጡ ‹‹ተቃራኒ ዝንባሌዎች›› ምክንያት በጎ ሥራዎችን ከመለማመድ ይደናቀፋል። በሌላ አነጋገር፣ የመለማመጃ ዘዴዎቹ የእነዚህን የበጎ ባህርያት ተግባር ሊያደናቅፉ ቢችሉም፣ የበጎ ሥራዎች ውስጣዊ አንድነት ሁል ጊዜ የግድ የሚገኘው በባህርይ ውስጥ ነው። ስለዚህ፣ ‹‹ሰዎችን ደረጃ በደረጃ ምስጢሩን ሙሉ በሙሉ እንዲቀበሉ የሚያስተዋውቅ ስነ ትምህርት›› ያስፈልጋል። ግለሰቦች በእውነት ነጻና ኃላፊነት የሚሰማቸው ውሳኔዎችን ወደሚወስኑበት የብስለት ደረጃ ለመድረስ ብዙ ጊዜ ትዕግሥትን ይጠይቃል። ቅዱስ ጴጥሮስ እንዳለው ‹‹ጊዜ የእግዚአብሔር መልእክተኛ ነው››።

በእግዚአብሔር ዘንድ ያለው የእያንዳንዱ ሰው አቋምና በጸጋ ያለው ሕይወት ከውጭ ሆኖ ሙሉ በሙሉ የማያውቃቸው ምስጢሮች እንደሆኑ ከሌሎች ጋር አብሮ የሚጓዝ ሰው መገንዘብ አለበት። ወንጌል ሌሎችን እንድናርምና የሥራቸውን ተጨባጭ ከፋት እንዲያውቁ መርዳት (ንጽ.ማቴ.18፡15)፣ ነገር ግን ስለ ኃላፊነታቸውና ተወቃሽነታቸው ፍርድ እንዳንሰጥ (ንጽ.ማቴ.7፡1፤ሉቃ.6፡37) ይነግረናል። በዚህ መልካም ጉዞ የተካነ ሰው በተስፋ መቁረጥ ወይም በፍርሃት አይሸነፍም። ሌሎችን ከበሽታቸው እንዲፈወሱ፣ አልጋቸውን እንዲሸከሙ፣ መስቀልን እንዲይዙ፣ ወንጌልን ለመስበክ ሁሉን ከኋላቸው ትተው በአዲስ መንፈስ ወደ ፊት እንዲጓዙ ይጠሯቸዋል። አብሮ የመጓዝና የመረዳት፣ እንዲሁም አብረውን ለሚጓዙ ሰዎች ክፍት የመሆን የግል ተሞክሮአችን ሌሎችን እንድንታገሥና እንድንራራላቸው፣ የእነርሱንም ተአማኒነት፣ ግልጽነትንና ለማደግ ያላቸውን ዝግጁነት ለማግኘት የሚያስችለንን ትክክለኛ መንገድ ያስተምረናል።

እውነተኛ መንፈሳዊ አብሮ ተጓዥነት ሁል ጊዜ የሚጀምረውና የሚዳብረው ለስብከተ ወንጌል ተልእኮ ባለው አገልግሎት መሠረት ነው። ጳውሎስ ከጢሞቴዎስና ከቲቶ ጋር የነበረው ግንኙነት በሐዋርያዊ ሥራ ውስጥ ለሚፈጸመው ለዚህ የጋራ ጉዞና ሕንጸት ምሳሌ ይሆነናል። ጳውሎስ ‹‹ገና ያልተስተካከለውን ነገር ለማስተካከል›› (ቲቶ 1፡5፤ ንጽ 1 ጢሞ. 1፡3-55) በየከተማው የሚቆዩበትን ተልእኮ ሲሰጣቸው፣ ለግል ሕይወታቸውና ለሐዋርያዊ ሥራቸው የሚሆኑ ትእዛዞችንም ሰጣቸው። ይህ ከማናቸውም ዓይነት የጉዞ ላይ ጣልቃ ገብነት ወይም የተናጠል የግል ስኬት በግልጽ ይለያል። የወንጌል ልኡካን ደቀ መዛሙርት ከወንጌል ልኡካን ደቀ መዛሙርት ጋር አብረው ይጓዛሉ።

### በእግዚአብሔር ቃል ላይ ማተኮር

ስብከት በእግዚአብሔር ቃል የዳበረ ብቻ መሆን የለበትም። የወንጌል ስብከት ሁሉ በዚያ ቃል ላይ የተመሠረተ፣ የተደመጠ፣ የተተነተነ፣ የተኖረበት፣ የተከበረና የተመሰከረለት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የስብከተ ወንጌል ዋና ምንጭ ነው። ከዚህም የተነሣ ቃሉን በመስማት ረገድ ያለማቋረጥ መሰልጠን ያስፈልገናል። ቤተ ክርስቲያን ራስዋ ያለመታከት በስብከተ ወንጌል ካልታነጸች ወንጌልን አትሰብክም። በመሆኑም፣ የእግዚአብሔር ቃል ‹‹ምን ጊዜም የቤተ ክርስቲያን ተግባር ሁሉ መሠረት›› እንዲሆን የግድ ይላል። ከሁሉ በላይ በመሥዋዕተ ቅዳሴ ወቅት የተደመጠና የተከበረ የእግዚአብሔር ቃል ክርስቲያኖችን ይመግባል፣ ከውስጥም ያበረታቸዋል፣ በዕለታዊ ኑሮ ውስጥ እውነተኛ የወንጌል ምስክሮች እንዲሆኑ ያስችላቸዋል። በቃልና በምሥጢር መካከል ከነበረው ተጻራሪ አቋም ከራቅን ቆይተናል። ሕያውና ውጤታማ የሆነ የቃል ስብከት ቅዱስ ምሥጢርን ለመቀበል ያዘጋጃል፣ በምሥጢርም ያ ቃል ከፍተኛ ውጤታማነት ይኖረዋል።

የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ለማንኛውም አማኝ የተከፈተ በር መሆን አለበት። የተገለጠው ቃል የምናስተምረውን ትምህርተ ክርስቶስና እምነትን ለማስተላለፍ የምናደርገውን ጥረት ሁሉ በእጅጉ ያዳብረዋል። ስብከተ ወንጌል የእግዚአብሔርን ቃል በሚገባ ማወቅን ይጠይቃል፤ በመሆኑም ሰበካዎች፣ ቁምስናዎችና ካቶሊካዊ ማህበራት መጽሐፍ ቅዱስን በትጋትና በቀጣይነት ለማጥናት ሁኔታዎችን ማመቻቸት ይኖርባቸዋል፤ ከዚሁ ጋር የግልና የጋራ የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብና ጸሎት መበረታታት ያስፈልጋቸዋል። እግዚአብሔርን በጭፍን አንሻም፣ ወይም እርሱ አስቀድሞ እስኪናገረን አንጠብቅም፤ ምክንያቱም ‹‹እግዚአብሔር አስቀድሞ ተናግሮአል፣ ያልተገለጠልንና በተጨማሪ ማወቅ የሚያስፈልገን አንዳችም ነገር የለም››። ስለዚህ፣ ከተገለጠው ቃል የተገኘውን የላቀ ሀብት እንቀበል።

### የስብከተ ወንጌል ማኅበራዊ ገጽታ

ወንጌልን መስበክ በዓለማችን የእግዚአብሔርን መንግሥት መመሥረት ነው። ሆኖም ‹‹የስብከተ ወንጌል እውነታንና ሙላት፣ ውስብስብነትና ኃይል በከፊል ወይም በተበጣጠሰ መልኩ ለመተርጎም መሞከር ምስጢሩን የማዳከም ብሎም የማጥፋት አደጋ አለው››። ስለዚህ፣ አሁን ደግሞ ስለ ስብከተ ወንጌል ማኅበራዊ ገጽታ ያለኝን ጭንቀት ለማጋራት እፈልጋለሁ፤ ምክንያቱም ይህ ገጽታ በሚገባ ጎልቶ ካልወጣ የስብከተ ወንጌል ተልእኮን እውነተኛና ምሉእ ትርጉም የማዛባት ሥጋት አለና።

***ምንጭ፡*** *ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ፍራንቸስኮስ የወንጌል ደስታ በሚል አርዕስት በዛሬው ዓለም ወንጌልን ስለመስበክ ለጳጳሳት፣ ለካህናት፣ ለደናግል እና ለምዕመናን ይፋ ካደረጉት ሐዋርያዊ ምክር ከአንቀጽ 169-176 ላይ የተወሰደ።*

# የ‹ጥንዶች ለክርስቶስ›› ሱባኤ በሐዋሳ አገረ ስብከት ተካሄደ

ነሐሴ 3-5/2016ዓ.ም በክርስቶስ ትህትና እና ተአዝዞ ላይ ያተኮረ ሱባኤ በሐዋሳ አገረ ስብከት ተካሄደ። ሱባኤው ክርስቶስ ኢየሱስ ያሳየው ትሕትና በእኛም ዘንድ ሊኖር እንደሚገባ የሚያሳስበንን ወደ ፊልጵስዮስ የተጻፈው (ፊሊጵስዮስ 2:6-7 ) እንዲህ በሚለው መልእክት ያተኮረ ነበር፣ “በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረ ይህ አሳብ በእናንተ ዘንድ ደግሞ ይሁን። እርሱ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባ ነገር አልቈጠረውም፥ ነገር ግን የባሪያን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ፥ በምስሉም እንደ ሰው ተገኝቶ ራሱን አዋረደ፥ ለሞትም ይኸውም የመስቀል ሞት እንኳ የታዘዘ ሆነ።”

ከሐዋሳ ከሆሳእና ከመቂ እና ከአዲስ አበባ ሰበካዎች የተውጣጡ ከ120 በላይ የሆኑ ‹ጥንዶች› (Couples for Christ/CFC/ ጥንዶች ለክርስቶስ) የተሳተፉበት ሱባኤ በሓዋሳ አገረ ስብከት በሐዋሳ ከተማ በኢየሱስ ቅዱስ ልብ ቤተ ጸሎት ተካሂዷል።

ከሐዋሳ አገረስብከት (ከሐዋሳ፤ ሚቄ፤ ቱሎ፤ ዶንጎራ፤ ዲላ) ከሆሳእና አገረ ስብከት (ሆሳና፤ሰዳማ፤ዋሰራ፤ ዶዮገና ጃጁራ) ከመቂ ሀገረስብከትና ከአዲስ አበባ ሀገረስብከት (ናዝሬት) ተሳታፊዎችና የጥንዶች ለክርስቶስ መንፈሳዊ አባት የሆኑት ክቡር አባ አብነት አበበ በተገኙበት ሱባኤውን በመስዋእተ ቅዳሴ የከፈቱልን ክቡር አባታችን አባ ሁዋን የሐዋሳ አገረ ስብከት ሓዋርያዊ አስተዳዳሪ ነበሩ።

በሱባኤው ላይ የክርስቶስ ትህትና በእኛም ዘንድ ሊኖር እንደሚገባ በክቡር አባ አብነት ሰፊ አስተምህሮ ተሰጥቷል፤ በተለያዩ ግለሰቦችና ጥንዶችና በትህትናና በታዛዥነት ዙሪያ ላይ ያጠነጠኑ መንፈሳዊነቶችና ትንሽዋ ቤተክርስቲያን ስለሆነቸው ስለ ቤተሰብ አስፈላጊነት አስተምሮ ተላልፏል። ከእነኚህም መካከል ከኬንያ ናይሮቢ ተወክለው የመጡ ሚስተር ኒኮላስና ባለቤቱ ናንሲ፣ፖላንዳዊት ወ/ሮ ማግዳሌና ሶቦቃ ባለቤቷ ተስፋልደት፣ አቶ ደሳለኝ ለራጎና ባለቤታቸው ራሄል ኢላላ በምስክርነቱና በአስተምህሮው ተሳትፈዋል። እንዲሁም ከየሰበካው የመጡ መሪዎች የክርስቶስን ምሳሌ በመከተል የእግር አጠባ አካሂደዋል።

በመጨረሻም “እኔና ቤቴ እግዚአብሔር ግን እንመልካለን እናንተ የምታመልኩትን ዛሬውኑ ምረጡ የሚል ትምህርት በክርስቶስ ጥንዶች ማህበር መሪ አቶ ተስፋልደት ሌሊሾ የተሰጠ ሲሆን ሁሉም ጥንዶች ቤት ክርስቲያንን ለማገልገል ቃል ገብተዋል።

በመጨረሻም ክቡር አባ አብነት የሱባኤው መዝጊያ የሆነውን መስዋእተ ቅዳሴ በመምራትና ቃለ ምእዳን በማሰማት ካጠናቀቁ በኋላ ክቡር ቆሞሱን አባ አልቴሳንና ለሱባኤው መሳካት የተባበሩ አካላትን ከልብ አመስግነዋል።

ይህ ዓምድ በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያንን የጳጳሳት ጉባኤ ጠቅላይ ጽ/ቤት ከፍትህና ሰላም ክፍል ጋር በትብብር የሚዘጋጅ ነው።

**ኃጢአት ወደ ዓለም ገብቶ ሞትን ያመጣብን በመብል ምክንያት ነው። (ዘፍ.3፥1-24)**



በክቡር አባ አብነት አበበ
ዘማኅበረ ልኡካን/ ላዛሪስት

# ምስክሮቼ ትሆናላችሁ

ካለፈው ዕትም የቀጠለ

## የግል ምስክርነት ምን ማለት ነው?

የግል ምስክርነትህ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እንዴት እንዳወቅኸው የሚያሳይ ነው፤ ጌታ ኢየሱስ ሕይወትህን እንዴት እንደቀየረው ስትመሰክር ማንም ትክክል አይደለህም ብሎ ሊቃወምህ አይችልም ምክንያም የምታውቀው አንተ ብቻ ነህና በመሆኑም ግለ ምስክርነትህ አምላክ ከሆነው ከክርስቶስ ጋር ያለህን ወዳጅነት የሚገልጽ ነው። በምስክርነትህ ክርስቶስን ነው የምታጎላው የምታከብረው፤ ይህም ስለ ወንጌሉ ብዙ ይናገራል። ምስክርነትህ ስለ ኢየሱስ ማንነት (ኢየሱስ ማነው የሚለው) ብቻ ሳይሆን እርሱ በሕይወትህ ስለሰራቸው ነገሮች ጭምር የሚመሰክር ነው፤ ይህንንም የምታካፍለው በቅንዓትና በትህትና እንዲሁም ምሥጋና በተሞላበት መንፈስ ስለሚሆን ሰዎችን ይነካል።

ለአንዳንድ ሰዎች ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስና ስለ ቤተክርስቲያኑ ሲነገር (ሲመሰከር) ካልሰሙ ምስክርነት የሚለው ነገር ላይገባቸውና አንተም እንዴት እንደተቀየርክ እስካልመሰከርክ ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ የሚለው ቃል ትርጉም ላይሰጣቸው ይችላል። ስለዚህ ያንተ ምስክርነት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለው የድኅነትን/የመዳን/ ታሪክና የኢየሱስ ክርስቶስ ጌትነትን እውነተኛ ያደርገዋል፤ ጌታ በግለሰብ ደረጃ ጌትነቱን እንደሚገልጽ ያሳያል። በጎነት (መልካምን ማድረግ) እና ሁሌም በእግዚአብሔር ፊት መሆንን መለማመድ እጅግ አስፈላጊ ነው፤የግል ቅድስናህ (መልካም አብነት መስጠትህ) ምስክርነትህን እንዲያምኑት ያደርጋል።

## የእግዚአብሔርን ፍቅር ለሌሎች ለመንገር አምስት መንገዶች፡-

ምስክርነት ስንል ስለወደደንና ስለሚወደን አምላክ ስለ እርሱ ፍቅር መናገር ማለት ነው። ስለ ጌታ ኢየሱስ ፍቅርና እሱን ያገኘህበት/የተዋወቅህበት/ መንገድና ስለሰራልህ ድንቅ ሥራዎቹ ለመመስከር የሚረዱህ አምስት መንገዶችን እነሆ። የሚመችህን መምረጥ ትችላለህ። ነገር ግን ምስክርነትን ለመስጠት ያሉን መንገዶች እነኚህ አምስቱ ብቻ ናቸው ማለት እንዳልሆነ ልብ ይሏል።

**1. ከእግዚአብሔር ጋር ያደረኩት ጉዞ**

በግልህ ከእግዚአብሔር ጋር የተጓዝኸውን መንገድ ምን እንደሚመስል መመስከር።

**2. ካቶሊክ በመሆኔ ደስ የምሰኝባቸው ምክንያቶቼ**

ካቶሊክ በመሆንህ የምትደሰትባቸው ምክንያቶች ምን ምን እንደሆኑ በመጥቀስ ማብራራት።

**3. ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን በክርስቶስ ኢየሱስ ስለመመሰረቷ**

ካቶሊካዊት ቤተክርቲያን የተመሰረተችው በክርስቶስ ስለመሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ያለውን እውነታ በማቅረብ ማስረዳት።

**4. የተለወጥኩበትን ታሪክ መተረክ።**

እግዚአብሔር እንዴት ወደ ሕይወቴ ገብቶ እንደለወጠኝ መመስከር፤ ወይም ደግሞ እንዴት ካቶሊክ እንደሆንኩ ምስክርነት መስጠት።

**5. የእግዚአብሔር ጥሪ እና የእኔ ጥሪ**

እግዚአብሔር በተለያዩ መንገዶች ሰዎችን ወደ ደህንነት ይጠራል፤ የምትኖረው በጋብቻ ሕይወት ውስጥ ከሆነ እግዚአብሔር እንዴት የትዳር አጋርህን እንደሰጠህ የምትኖሩትን የፍቅር ሕይወት ማካፈል፤ የምትኖረው የምንኩስና ሕይወት ውስጥ ከሆነ እንዴትና ለምን ወደ ምንኩስና ኑሮ እንደገባህ መመስከር።

## የመለወጥ ታሪክ

በየትኛውም መንገድ መስክር ዋናው ነገር አቀራረቡን ቀለል አድርገው፤ አንድ ክስተት ላይ ትኩረት አድርግ። ለምሳሌ፡ እንዴት ከጥላቻ ወደ ፍቅር (ከ...ወደ....) እንደተለወጥክ መስክር። ከጥላቻ ወደ ፍቅር (አንዳንድ ሰዎችን እጠላ ነበር፣ አሁን ግን መውደድ ጀምሬአለሁ)፤ከሃዘን ወደ ደስታ፣ ከተስፋ መቁረጥ ወደ መጽናናት፣ ከቁጣ ወደ ደስታ፣ ከድክመት ወደ ብርታት፣ ትርጉም አልባ ኑሮ ከመኖር ለዓላማ ወደመኖር፣ከጥፋተኝነት ስሜት ስህተቴን ወደ መቀበል፣ ከባርነት ወደ ነጻነት፣ ከብቸኝነት ወደ አብሮነት/ማኅበረሰባዊነት/፣ ከአመጸኝነት ወደ ታዛዥነት...የተለወጥኩበትን መንገድ ማሳየት።

## የምስክርነት ሶስት ገጽታዎች

ምስክርነትህን ስትሰጥ በሶስት ክፈለው፤ ማለትም ሕይወትህ፡ ጌታ ኢየሱስን ከማግኘትህ በፊት (ሕይወትህን ለእግዚአብሔር አሳልፈህ ከመስጠትህ በፊት)፣ እሱን ባገኘኸው ጊዜ (እግዚአብሄር በሕይወትህ እንዴት ጣልቃ እንደገባና እንደለወጠህ)፣ እሱን ካገኘኸው በኋላ (ያንተ አዲስ ሕይወት በክርስቶስ ኢየሱስ) ምን እንደሚመስል መመስከር።

**1. ሕይወትህን ለእግዚአብሔር ከመስጠትህ በፊት ያለው ታሪክ**

የቤተሰቦችህ ታሪክ-አስተዳደግህ-ጥሪህ-የሚያስደስቱህ ነገሮች.....ወዘተ...በተለይም ስላለፈው ሕይወትህ (ራስህን ለክርስቶስና ለቤተክርስቲያኑ ከመስጠትህ በፊት የነበረውን/ሐ.ሥ. 22፡1-5፣ 26፡4-5) መመስከር። ስላለፈው የኃጢአት ሕይወትህ ሮማንቲክ/ማራኪ/ ሳታደርገው መገለጽ ባለበትና በሚስብ መልኩ እውነቱን ተናገር። (ሐ.ሥ.26፡9-11)

**2. የእግዚአብሔር ‹‹መለኮታዊ ወረራ›› እና ያንተ የመለወጥ ታሪክ**

ካርዲናል ፉልተን ሺን ሲናገሩ የክርስቶስ መወለድ በሁለት መንገድ ነው ይላሉ፡ አንደኛው በዚህ ዓለም ላይ በቤተልሄም መወለድ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ አንዲት ነፍስ በመንፈሳዊነት እንደገና ስትወለድ ነው ጌታ ኢየሱስ ሁለተኛ ተወለደ የሚባለው። ሁለቱም የሚከናወኑት አምላክ ‹መለኮታዊ ወረራ› ሲያደርግ ነው። ስለዚህ እንዴት ነው በሕይወትህ ውስጥ «መለኮታዊ ወረራ» የተካሄደው? ማለትም ክርስቶስ እንዴት ነው ወደ ሕይወትህ ውስጥ የገባው፣ የሆነውን ስትመሰክር የምትናገረው ስላንተ ቢሆንም ዋናው ገጸ ባህሪ ግን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን አትዘንጋ። ትኩረትህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላይ ይሁን። ባንተ ሕይወት ውስጥ ያለውን ቦታና ከእርሱ ጋር ስለጀመርከው አዲሱን ግንኙነት/ወዳጅነትህን/ መስክር።

የምስክርነትህ ዋናው ቁልፉ (ቁም ነገሩ) ክርስቶስ ኢየሱስ በእግዚአብሔር የጸጋ ምስጢራት አማካኝነት በሰጠህ/በተቀበልከው/ ጸጋ አማካይነት እንዴት በእርሱ (በክርስቶስ) አዲስ ፍጥረት እንደሆንክ ማሳየት፡ ሕይወትህ እንዴት እንደተለወጠ መናገር ነው፤ «ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ፥ ሁሉም አዲስ ሆኖአል»(2ቆሮ. 5፡17)፤ (ሐ.ሥ 26፡12-19)።

**3. በክርስቶስ ኢየሱስ ያገኘኸው አዲስ ሕይወት**

አሁን «የክርስቶስ ልብ» አለህና (1ቆሮ. 2፡16) የዛሬው ሕይወትህ ከትናንት ሕይወትህ የተለየበትን መንገድ መግለጽ። የመለወጥህ ታሪክ ወደ ቤተክርስቲያን መምጣትህን ወይም እምነትን ወደመኖር/ወደመተግበር/ ውስጥ መግባትህ፡ የምትመሰክርለትን ሰው አሳምኖ አንተ ያገኘኸውን ከክርስቶስ ጋር ያለህን ወዳጅነት ይመኝ ዘንድ ማድረግ አለበት። በክስቶስ ኢየሱስ ስላገኘኸው አዲስ ሕይወት አጋንነህ አታውራ ምክንያቱም ሕይወት በመከራዎች በሙከራዎችና በስቃዮች የተሞላች ናትና። «ያለ ስቅለተ ዓርብ፡ የፋሲካ እሁድ የለም» (ሊቀ ጳጳስ ፉልተን ሺን)።

«ለእኛም ይገለጥ ዘንድ ካለው ክብር ጋር ቢመዛዘን የአሁኑ ዘመን ሥቃይ ምንም እንዳይደለ አስባለሁ።» (ሮም. 8፡18)። አሁን ክርስቶስን በመልበስህ (ገላ. 3፡27) ያገኘሃቸውን በረከቶች/የሚገኙትን በረከቶች/ጥቅሞች/ ተናገር። ለምሳሌ፡-ስለ ሕይወት ያለህ አዲስ አመለካከት፣ ይቅርታን ለማድረግ ያለህ ችሎታ/አቅም፣አዲሱ ነጻነትህ (ለምሳሌ፡-ከሱስ ወይም ከመጥፎ ልማድ መላቀቅህ በተለይ ደግሞ ከኃጢአት ባርነት ከሰይጣን እሥራት ነጻ መውጣትህ መስክር)።ዋና ዓላማው ክርስቶስ ኢየሱስን መስበክና እርሱን በቤተክርስቲያኑ ምስጢራት አማካኝነት በግል እንዴት ሊገኝ እንደሚችል ማሳየት ነው።

«በወንጌል አላፍርምና፤ አስቀድሞ ለአይሁዳዊ ደግሞም ለግሪክ ሰው፥ ለሚያምኑ ሁሉ የእግዚአብሔር ኃይል ለማዳን ነውና።» (ሮም. 1፡16)፤«የእግዚአብሔር መንግሥት በኃይል ነው እንጂ በቃል አይደለምና።» (1ቆሮ. 4፡20)፤ «ዳሩ ግን ጌታን እርሱም ክርስቶስ በልባችሁ ቀድሱት። በእናንተ ስላለ ተስፋ ምክንያትን ለሚጠይቁዋችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት ዘወትር የተዘጋጃችሁ ሁኑ፥ ነገር ግን በየዋህነትና በፍርሃት ይሁን።» (1ጴጥ. 3፡15)።

«ሰዎች ሁሉ የሚያውቁትና የሚያነቡት በልባችን የተጻፈ መልእክታችን እናንተ ናችሁ። እናንተም በሕያው እግዚአብሔር መንፈስ እንጂ በቀለም አይደለም፥ ሥጋ በሆነ በልብ ጽላት እንጂ በድንጋይ ጽላት ያልተጻፈ፥ በእኛም የተገለገለ የክርስቶስ መልእክት እንደ ሆናችሁ የተገለጠ ነው።» (2ቆሮ. 3፡2-3)። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፥ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ።» (ሐ.ሥ. 1፡8)።

## ስለ ክርስቶስ ስትመሰክር ማድረግ ያለብህና የሌለብህ ነገሮች በአጭሩ

ምስክርነትህ በመንፈስ ቅዱስ የተሞላና የሚያመለክተውም ወደ ዘላለማዊ ሕይወት መሆኑን እያወቅህ የሚከተሉተን ማድረግ ያለብህንና የሌለብህን ዝርዝሮች ማስታወስ አስፈላጊ ነው።

## ስለክርስቶስ ስትመሰክር ልታደርግ የሚገቡ ነገሮች እነሆ

- መንፈስ ቅዱስ ይመራህ ዘንድ ራስህን ለመንፈስ ቅዱስ ክፍት አድርግ እንጂ በሰብዓዊ ስጦታዎችህ ብቻ አትተማመን።
- ከክርስቶስ ጋር ስላለህ ወዳጅነት ተናገር።
- ክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ሕይወትህ የመጣው/የገባው/ በቤተክርስቲያን አማካኝነት መሆኑን በግልጽ ተናገር።
- በምስጢራት አማካኝነት በተቀበልካቸው ጸጋዎች መንፈስ ቅዱስ እንዴት በሕይወትህ እየሰራ እንደሆነ መስክር።
- ለምስክርነትህ የሚጠቅሙ የተወሰኑ ታሪኮችህን አዘጋጅ።
- አገላለጽህ በሰዎች አእምሮ ውስጥ እንዲቀር ስእላዊ አድርጋቸው።
- ከክርስቶስና ሙሽራው ከሆነችው ከቤተክርስቲያኑ ጋር ያለህ ግንኙነት (ቃልኪዳናዊ ሕብረት) እንዲጠነክር በየለቱ ጸልይ።
- አድማጮችህ እነማን እንደሆኑ ለይተህ እወቅ፤ የምታቀርብበት መንገድ እንደ ማንነታቸው ይሁን።
- የምታቀርባቸው ምሳሌዎች ከሕይወትህ ጋር የተያያዙና አድማጮችህን የሚወክሉ አድርጋቸው።
- ምስክርነትህ (ስትናገር) በድፍረትና በመተማመን ይሁን።
- ምስክርነትህን በሚማርክ/በሚስብ መልኩ አቅርበው።
- ሁሉንም ነገር መናገር ግዴታ ስላልሆነ ብዙ ነገሮች ልታልፋቸው እንደሚገባ እወቅ።
- የምታናግረውን ሰው ፊት ለፊት እያየህ (ዓይኑን እየተመለከትህ) እያየህ፣ በስሙ እየጠራህ፣ ትኩረትህን እንደሰጠኸው ያውቅ ዘንድ አድርግ።
- የማይሆን ቀልድ (ራስን ዝቅ የሚያደርግ...) እንዳትቀልድ ተጠንቀቅ።
- ስለክርስቶስ ስትመሰክር ልታደርግ የማይገቡ ነገሮች እነሆ
- ሁሉንም አውቃለሁ ዓይነት ሰው አትሁን።
- ምስክርነቱን አታንዛዛው (አላስፈላጊ ነገሮችን አስወግድ)
- አትውቀስ፣አትገስጽ፣ ስለሌሎች ክፉ ነገር አትናገር፤ (ለምሳሌ፡- ስለ ካህናት፡ ስለ ወላጆች፡ ስለ መምህራን፣ ስለ ቤተክርስቲያን...በጎ ያልሆኑ አድራጎቶች... አትናገር..)።
- ያለፈው መጥፎ የምትለው የህይወትህን ክፍል/ኃጢአተኛነትህን/ አታጋነው (ማራኪ አታድርገው)

ወደ ገፅ 11 ዞሯል

ይህ ዓምድ በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያንን የጳጳሳት ጉባኤ ጠቅላይ ጽ/ቤት ሐዋርያዊ ሥራዎች ኮሚሽን ጋር በትብብር የሚዘጋጅ ነው

**“እውነት እውነት እላችኋለሁ የሰውን ልጅ ሥጋውን ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም። ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው፤” ሲል አረጋግጦልናል። (ዮሐ.6፥53-54)**



በክቡር አባ ፊሊጶስ ደንድር
ከሀገረ ቫቲካን ሮም

# የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የመስቀሉ ትሩፋቶች



ጌታችንና አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ተሰቅሎ ቅዱስ ሥጋውን ቆርሶልናል፥ ክቡር ደሙን አፍስሶልናል፥ ነፍሱንም በፈቃዱ አሳልፎ ሰጥቶልናል። ይህንንም ያደረገው በቤዛነቱ እኛን ከእርግማን ሊዋጀን ነው። ምክንያቱም የሰው ልጆች በጠቅላላ በመርገመ ሥጋ በመርገመ ነፍስ ተይዘን ነበርና። በመሆኑም በሞተ ሥጋ ላይም ሞተ ነፍስ ተፈርዶብን ከእርግማን በታች ወድቀን ነበር። ይሁን እንጂ ፈጣሪያችን እኛን ለመፈለግ ከሰማየ ሰማያት ወረደ። (ማቴ.18፥12-14)። በመንፈስ ቅዱስ ከድንግል ማርያም ተፀነሰ (ሉቃ.1፥35) በከብቶች በረት ተወለደ። (ሉቃ.2፥7፤) አምላክ ሰው ሆነ። ቀስ በቀስም አደገ። (ሉቃ.2፥40)። በሠላሳ ዓመት እድሜው በፈለገ ዮርዳኖስ በዮሐንስ መጥምቅ ከተጠመቀ በኋላ አርባ ቀንና ሌሊት ጾመ። (ማቴ.3፥13-17)። ከዚያም አሥራ ሁለቱን ደቀ መዛሙርት ሰባ ሁለቱን አርድዕትና ሠላሳ ስድስቱን ቅዱሳት አንስት መረጠ። (የሐሥ.1፥15)። አዲስ ሕግ ወንጌልንም ሦስት ዓመት ከሦስት ወር አስተማረ። በመጨረሻም ስለእኛ ኃጢአት ተላልፎ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሞተ። (ማር.15፥23-37)። የሞተውም በፈቃዱ ነው። (ዮሐ.10፥11፤ 15፥13)። በዚህም የማዳን ሥራ በመስቀል ላይ ፈጸመው። (ዮሐ.19፥30)።

እንግዲህ ጌታችን ወደዚህ ዓለም መጥቶ በመልዕልተ መስቀል ተሰቅሎ የሞተው ከላይ እንደተጠቀሰው ስለ እኛ እርግማን ተላልፎ ነው። እርሱ በመስቀል ላይ ኃጢአታችንን ስለተሸከመልንም እኛ ከእርግማን ከመርገመ ሥጋ፥ ከመርገመ ነፍስ ነፃ ሆነናል። ነቢዩ ኢሳይያስ በትንቢቱ "በእውነት ደዌያችንን ተቀበለ፥ ሕመማችንንም ተሸከሚል፤ ... እርሱ ግን ስለመተላለፋችን ቆሰለ፥ ስለበደላችንም ደቀቀ፤ የደኅንነታችንም ተግሣፅ በእርሱ ላይ ነበረ፥ በእርሱም ቁስል እኛ ተፈወስን።" ሲል አስቀድሞ የተናገረው ለዚህ ነው። (ኢሳ.53፥4-5)። ቅዱስ ጳውሎስም ለገላትያ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ "በእንጨት የሚሰቀል ሁል የተረገመ ነው ተብሎ ተጽፏልና፥ ክርስቶስ ስለ እርግማን ሆኖ ስለ እኛ ኃጢአት ተላልፎ በመስቀል ከሕግ እርግማን ዋጀን፤" ብሏል። (ገላ.3፥13)። በመልእክቱም "የእግዚአብሔር ማደሪያ ለመሆን እኛን ጻድቃን ያሰኘን ዘንድ ስለ እኛ ኃጢአት ተላልፎ ራሱን ኃጥእ አሰኝቷልና፤" ብሏል። (2ኛ ቆሮ.5፥21)። ከዚህም ሌላ ለፊሊጵስዩስ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ "ነገር ግን የባርያን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ፥ በምስሉም እንደ ሰው ተገኝቶ ራሱን አዋረደ፥ ይኸውም ለመስቀል ሞት እንኳ የታዘዘ ሆነ፤" ብሏል። (ፊል.2፥7-8)። ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስም በበኩሉ "እርሱ ኃጢአት አላደረገም፥ ተንኰልም በአፉ አልተገኘበትም፤ ሲሰድቡት መልሶ አልተሳደበም መከራንም ሲቀበል አልዛተም፥ ነገር ግን በጽድቅ ለሚፈርደው ራሱን አሳልፎ ሰጠ፥ ኃጢአታችንን /እርግማናችንን/ በእንጨት በመስቀል ላይ ተሸከመ፤ በመገረፉ ቁስል ተፈወሳችሁ፤" ብሏል። (1ኛ ጴጥ.2፥22-24)። በመሆኑም በመስቀል ላይ በተፈጸመው ቤዛነት ብዙ ነገር አግኝተናል።

## የክርስቶስ መስቀል ዘላለማዊ ሕይወትን ሰጥቶናል

በኃጢአት ምክንያት ሞት ገዝቶን ሞት ነግሦብን ነበር በመሆኑም (ሮሜ.5፥12-14)። ከክርስቶስ በኋላ ግን በክርስቶስ ቤዛነት ሞት ስለተሻረ አጥተነው የነበረውን ሕይወት አግኝተናል። ለዚህም ነው "ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ ሁሉ በክርስቶስ ደግሞ ሕያዋን ይሆናሉና፤" የተባለው። (1ኛ ቆሮ.15፥22)። በተጨማሪም "እኛ ሁላችን ደግሞ፥ በሥጋችን ምኞት በፊት እንኖር ነበር እንደሌሎቹም ደግሞ ከፍጥረታችን የቁጣ ልጆች ነበርን። ነገር ግን እግዚአብሔር በምሕረቱ ባለጠጋ ስለሆነ፥ ከወደደን ከትልቅ ፍቅሩ የተነሣ በበደላችን ሙታን እንኳ በሆንን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር በክርስቶስ ቤዛነት ሕይወትን ሰጠን።" ተብሏል። (ኤፌ.2፥3-5)። ምክንያቱም ጌታችን በሞቱ ሞትን ሽሯልና። (2ኛ. ጢሞ.1፥10)።

## በመስቀሉ የሕይወትን ምግብ የሆነው ቅዱስ ቁርባንን ሰጥቶናል

ኃጢአት ወደ ዓለም ገብቶ ሞትን ያመጣብን በመብል ምክንያት ነው። (ዘፍ.3፥1-24)። ምክንያቱም አዳምና ሔዋን የዕፀ በለስን ፍሬ በልተው ጐትተው ያመጡት ሞትን ነውና። ስለዚህ ሰው ከእርሱ በልቶ እንዳይሞት ሥጋውን የሕይወት እንጀራ አድርጎ በመስቀል ላይ ሰጠን። ይህንንም "እውነት እውነት እላችኋለሁ የሰውን ልጅ ሥጋውን ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም። ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው፤" ሲል አረጋግጦልናል። (ዮሐ.6፥53-54)። በመሆኑም ዕለት ዕለት በቤተክርስቲያን የሚሠዋውና በሃይማኖት የምንቀበለው ቅዱስ ቁርባን አማናዊ የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና አማናዊ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ነው። ምክንያቱም ኅብስቱ ተለውጦ ሥጋ መለኰት ወይኑም ተለውጦ ደመ መለኰት ይሆናልና። (ማቴ.26፥27-29)።

## የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ሰላምን አስገኝቶልናል

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡- "ሰላምን እተውላችኋለሁ፥ ሰላሜን እሰጣችኋለሁ፤ እኔ የምሰጣችሁ ዓለም እንደሚሰጥ አይደለም፤" ብሎ እንደተናገረ ፍጹም የሆነውን ሰላም የሰጠን በመስቀል ላይ ነው። ይህንንም፡- ሞትን በኃይሉ ድል አድርጎ በተነሣ ጊዜ "ሰላም ለእናንተ ይሁን፤" በማለት ለደቀ መዛሙርቱ አረጋግጦላቸዋል። (ዮሐ.14፥27፤ 20፥19፣26)። ይህንን በተመለከተ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "እግዚአብሔር ሙላቱ ሁሉ በእርሱ እንዲኖር፥ በእርሱም በኩል በመስቀሉ ደም ሰላም አድርጎ በምድር ወይም በሰማያት ያሉትን ሁሉ ለራሱ እንዲያስታርቅ ፈቅዷልና፤" በማለት የቆላስይስን ሰዎች አስተምሯል። ቆላ.1፥19-20። የኤፌሶንን ሰዎችም "አሁን ግን እናንተ በፊት ርቃችሁ የነበራችሁ በክርስቶስ ደም ቀርባችኋል። እርሱ ሰላማችን ነውና /ሰላማችን የተገኘው በእርሱ ቤዛነት ነውና/፤" ብሏቸዋል። (ኤፌ.2፥13)።

## የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል አዲስ ማንነት አላብሶናል

በመርገመ ሥጋ በመርገመ ነፍስ አርጅቶ የነበረው ሰውነታችን አዲስ የሆነው በመስቀል ላይ በተፈጸመው ቤዛነት ነው።

ወደ ገፅ 7 ዞሯል

ይህ ዓምድ በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያንን የጳጳሳት ጉባኤ ጠቅላይ ጽ/ቤት እና ከጤና ክፍል ጋር በትብብር የሚዘጋጅ ነው

**"በእንጨት የሚሰቀል ሁል የተረገመ ነው ተብሎ ተጽፏልና፥ ክርስቶስ ስለ እርግማን ሆኖ ስለ እኛ ኃጢአት ተላልፎ በመስቀል ከሕግ እርግማን ዋጀን፤" ብሏል። (ገላ.3፥13)**



በክቡር ካቲኪስት ወርቁ ጦጤ
ከኮንሶላታ ማርያም ቤተ ጸሎት

# ሕዋሳቶቻችን ባለመጠበቅና ባለመቆጣጠር የሚመጣብን ጉዳት

ሕዋሳቶቻችን የነፍሳችን ዋልታዎችና ማገሮች እንዲሁም በሮችና መስኮቶት ናቸው። አንደ ቤት አንድ ቤት አለዋልታዎችና ማገሮች አይሠራም። አለመዝጊያና አለመስኮት መልክና ቁም ነገር ስለማይኖረው ሰው ሊኖርበት አይችልም። እንደዚሁ ደግሞ ነፍሳችን በዚህ ዓለም ላይ ከሥጋችን ጋር ተዋሕዳ ሰትኖር ሕወሳት አሏት። እነዚህ ሕዋሳቶቻችን ለመንቀሳቀስና ማናቸውንም ሥራ ለመሥራት አገልጋዩቿ ናቸው።

ነፍሳችን ከሕዋሳቶቻችን መካከል በዓይናችን፣ በአፋችን፣ በጆሮአችን በልባችን፣ በአእምሮአችን፣ በእጆቻችን፣ በእግሮቻችን፣ አማካይነት የሚያስፍለጓትን አገልግሎቶች ታገኛለች፤ የድድቅ ፍሬም ትሰበሰብላች። ዓይኖቻችን ወደ እግዚአብሔር ይመሯታል፤ ትልቅነቱን፣ ደግነቱን፣ መሐሪነቱን፣ ኃያልነቱን፣ ቅንነቱን፣ እና የማይሳሳት ፍርዱን ይገልጡላታለ። የእግዚአብሔር ሥራዎች የሆኑትን የሥነ ፍጥረትን ውበትን በማሳየት በአፈጣጠራቸው ድነቅነትና በውበታቸው እግዚአብሔርን እንድትመለከት ያደርጋታል። የእግዚአብሔር ሥራዎች የሆኑትን የሥነ ፍጥረትን ውበትን በማሳየት በአፈጣጠራቸው ድንቅነትና በውበታቸው እግዚአብሔርን እንድትመለከት ያደርጋታል። አፍ ደግሞ ሃሳቧን፣ ምኞቷን፣ ጸሎቷን ወደ እግዚአብሔር በንግግር ያደርስላታል።

ነፍሳችን በአፋችን አማካይነት እግዚአብሔርን ታከብራልች፣ ታመሰግናለች። ጆሮአችን የእግዚአብሔርን ቃልና መንፈሳዊ ምክሮችን ሁሉ ይሰማሉ። ስለዚህ ሕዋሳቶቻችን ሁሉ ነፍስን ወደ ፈጣሪዋ ይመሯታል። የሠራናቸው ቤታችን መዝጊያዎችና መስኮቶች ካልጠበቁ ሰውን መጥቀማቸውንና ማገልገላቸው ይቅርና በራሳችን ላይ ጉዳት ያደርሱብናል። እንዲሁም ከፈጣያችን የሰጡን ሕዋሳቶቻችን በተገቢው መንግድ ካልጠበቅንና ካልተቆጣጠርናቸው ነፍሳችን ከመጥቀም ይልቅ ነፍሳችን ላይ ጉዳት ያደርሱባታል። ሕዋሳቶቻችን ክፍት አድረገን ብንተዋቸው ወይም ብንለቃቸው ነፍሳችን ትበላሻለች። ለክብርና ለምገስ ከፈጣሪ የተሰጡን ሕዋሳቶቻችን በአሳሳቹ ሰይጣን አማካይነት ወደ ውስጥዋ ገብቶ ያረክሳታል።

ነቢዩ ኤርሜያስ የእግዚአብሔርን ቃል እንዲህ ይለናል "ሞት በየመስኮቶቻችን ገብቶአል፣ በየቤተ መንግሥትታችንም ተገኝቶአል፣ ልጆችን በየመንግዱ፣ ጐልማሶችንም በየአደባባዩ ቀስፎአል" (ኤር. 9፡21)።

ኢዮብም የእግዚአብሔርን ቃል እንዲህ ይለናል "ጨለማ ወደ ሆነው ወደ ሙታን ዓለም የሚያስገቡት በሮች ተገልጠውለህ አይተናልን?" (ኢዮ. 38፡47)።

ሐዋርያው ቅዱስ ያዕቆብ በመልእክቱ የእግዚአብሔርን ቃል እንዲህ ይለናል "ከአንድ አፍ ምሥጋናና እርግማን ይወጣሉ፤ ወንድሞቼ ሆይ ይህ ሊሆን አይገባም። ከአንድ ምንጭ ጣፊጭ ውሃና መራራ ውሃ ሊወጣ ይችላልን?"(ያቆ. 3፡10-11)። ሐዋርያ ቅዱስ ያዕቆብ በሌላ በኩልም እንዲህ ይለናል "አንደበት እሳት ነው አንደበት የሚገድል መርዝ የሞላበት ወላዋይ ክፋት ነው" (ያቆ. 3፡6-8)።

አፋችን የማይረባና የማይጠቅም ነገር ሲናገር፣ ዓይናችን የማያስፈልግና የተከለከለ ነገር ሲያይ እንዲሁም ጆሮአችን ክፉ ንግግርን ሲሰማ ነፍሳችን በጣም ትጐዳለች፤ መንፈሳዊ ቅዝቃዜ በልባችን ውሰጥ ይገባል። ቀስ እያለም ከእግዚአብሔር እየራቅን ወደ ኃጢአት እንደርሳለን። ሕዋሳቶቻችንን በጥንቃቄ ባለመጠበቃችን በመንፈስ እንደምንጐዳ አስቀድመን እናውቃን። አብዛኛው ኃጢአታችን ሕዋሳቶቻችንን ሰብስበንና ጠብቀን ካለመያዛችን የተነሳ የሚመጡ መሆናቸው ሕሊናችን ይመሰክርብናል።

እንግዲህ ዓይናችን፣ ጆሮአችን፣ አፋችን… ባጠቅላይ ሕዋሳቶቻችን ሁሉ እንደፈለጉ የምንለቃቸው ከሆነ በኋላ ከፍ ያለ ሥቃይና መከራ ጭንቀት እንደሚያመጡብን አውቀን ለነፍሳችን እንዲጠቅሙ የተፈጠሩ ጥፋትና ጉዳት እንዳያመጡብን ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልገናለ። አለበለዚያ ዘለዓለም ሞተ ሊያደርሱባት ይችላሉ። እነዚህ የነፍሳችን አጋዦችና ረዳቶች እንዲሆኑ በጌታ የተመደቡ ሕዋሳቶቻችን በእኛ ቸልተኛነት ምክንያት አጥፊዎች ሆነው ይገኛሉ።

ቤቶቻችንእንዳይበላሹናእንዳይሰረቁበጥንቃቄ እንጠብቃለን። በሮችንና መስኮቶችንም ዘወትር ገደብ አልባ ክፍት አድረገን መተው ሳይሆን በሚያስፈልገው ጊዜ ብቻ እንደምንከፍተው፤፤ እንዲሁም ነፍሳችን በኃጢአት እንዳትረክስና በሰይጣን እንዳትወድቅ ከፈለግን የሕዋሳቶቻችን በሮችንና መስኮቶችን በጥንቃቄ ተቆጣጥረን በሚያስፈልግ ጊዜ ብቻ ከፍተን እንድንጠቅምባቸው ያስፈልገናል። አፋችን፣ ዓይናችን፣ ጆሮአችን እንዲሁም ሕዋሳቶቻችንን ሁሉ በቁጥጥራችን ሥር እናውላቸው። ክርስቶስን መምሰል የተባው መጽሐፍ "የሕዋሳቶቻችን በሮች በጥነቃቄ ካልጠበቃችሁ፤ ያን የሰበሰባችሁትን መልካም ነገር ሁሉ በጥቂት ጊዜ ውሰጥ ታጠፉታላችሁ" እያለ ሕዋሳቶቻችንን እንድንጠብቅና እነድንቆጣጠር ያስጠነቅቀናል።

ስለዚህ የተወደዳችሁ በክርስቶስ ደም አባቶቼና እናቶቼ ወንድሞቼና እህቶቼ ሆይ እግዚአብሔር አባታችን ሕዋሳቶቻችን የሰጠን እኛ በአገባቡ ተጠቅመንበት ለምሥጋና በክብር እንድንይዘው የተሰጡን የጽድቅ ስጦታዎች ናቸው።

ነገር ግን እግዚአብሔር የሰጠንን ሕዋሳቶቻችንን ሥጋችን በሚያዙን መንገድ በጊዜያዊ ስሜት ተነድተን የምንኳዝ ከሆን፤ ነፍሳችን በሞት ጐዳና እንዳለች "ሕሊናችን" ይወቅሰናል፤ ደግሞም ይመሰክርብናል። "ሕሊና" ማለት እግዚአብሔር በውስጣችን ያስቀመጠው የራሱ ዳኛ ነው።"ሕሊናችን" መልካም አድርገን ሕዋሳቶቻችንን በአግባቡ ስንጠቀምበት መንፈሳዊ ኩራትና ደስታ እንዲሰማን ያደርገናል። ይህ ሳይሆን ቀርቶ ሕዋሳቶቻችንን ለክፋትና ለተንኰል፣ ለኃጢአት ከተጠቀምንባቸው አይደለም ቀን ማታም ብንተኛም እንኳን ሕሊናችን እንቅልፍ ይነሳናል።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ከእግዚአብሔር የተሰጡትንን ሕዋሳቶቻችንን እንዴት አድርግን በሥጋችን መጠቀም እንዳለብን እንዲህ እያለ ይመክረናል። "ሁሉ ነገር ተፈቅዶልኛል ግን ሁሉም ነገር ይጠቅመኛል ማለት አይደለም፤ ሁሉም ተፈቅዶልኛል ይሁን እንጂ ለማናቸውም ነገር ባሪያ ሆኜ አልገዛም ምግብ ለሆድ ሆድም ለምግብ ነው፤ ታዲያ እኮ እግዚአብሔር ምግብንም ሆድንም ያጠፋቸዋል፤ ነገር ግን ሰውነታችን ለጌታ ኢየሱስ ጌታ ኢየሱስም ለሰውነታችን ስለሆነ ሰውነታችንን ለዝሙት ማዋል አይገባንም። እግዚአብሔር ጌታ ኢየሱስን ከሞት አስንሥቶታል እኛንም በኃይሉ ከሞተ ያስነሣናል።"

ሰውነታችሁ የክርስቶስ አካል ክፍል መሆኑን ታውቁ የለምን? ታድያ የክርስቶስን አካል ክፍል ወስጄ የአመንዝራ ሴት አካል ክፍል እንዲሆን ላደርገው ይገባልን? ከቶ አይገባም ከአመንዝራ ሴት ጋር በግብረ ሥጋ የሚተባበር ሰው ከእርሷ ጋር አንድ አካል መሆኑን ታውቆ የለምን? ምክንያቱም "ሁለቱም አንድ አካል ይሆናሉ" ተብሎ ተጽፏል።

ከጌታ ኢየሱስ ጋር የሚተባበር ሰው የሚያደርገው ሌላው ኃጢአት ሁሉ ከሰውነቱ ውጪ የሚደረግ ነው። ዝሙትን የሚፈጽም ሰው ግን በገዛ ሰውነቱ ላይ ኃጢአት ያደረጋል፤ ሰውነታችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁትና በውስጣችሁም የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ መሆኑን ታውቁ የለምን? እንግዲህ እናት የእግዚአብሔር ናችሁ እንጂ የራሳችሁ አይደላችሁም። ምክንያቱም እርሱ በዋጋ ገዝቶአችኋል፣ ስለዚህ በሰውነታችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ።" (1ቆሮ. 6፡12-20)።

የወደዳችሁ የእግዚአብሔር ቤተሰቦች ሆይ ከእግዚአብሔር የተሰጡን ሕዋሳቶቻችን ባለመጠበቅና ባለመቆጣጠር የሚመጣብን ጉዳት እግዚአብሔር የሚያመጣብን ሳይሆን እኛው በገዛ ፈቅዳችን በራሳችን በላይ የምናመጣው ጉዳት ነው። እግዚአብሔር አባታችን ለሕዋሳቶቻተን የተሰጠን በሥጋዊ ስሜት እየነዳን እግዚአብሔርን እንድናሳዝነው ሳይህን ስሜቶቻችን በተሰጠን መንፈሳዊ ጥበብንና ዕውቀትን ተጠቅመን በሰውነታችን እግዚአብሔርን እንድናከብርበት ነው። "ስሜት እኛን እንዲቆጣጠረን ሳይሆን እኛ ስሜትን እንድንቆጣጠረው" ለክብሩ የተጠራን ቅዱሳን ነን። ቅድስና የሚገኘው ደግሞ እኛ ኃጢአት ማድረግ እየቻልን እራሳችንን ከዚያ ኃጢአት ምንጭ በማስተዋል ስንርቅ ብቻ ነው። ስለዚህ ነው ሲራክ የእግዚአብሔርን ቃል እንዲህ የሚለን "ኃጢአት ማድረግ እየቻለ ኃጢአት የማያደርግ ሰው ቅዱስ ነው" (ሲራ. 31፡10)።

ዮሴፍ የጳጢፋር ሚስት ለዝሙት ስትጋብዘው ዝሙት መፈጸም ይችል ነበር። ምንያቱም በቤቱ ውስጥ ከእርሷና ከእርሱ ውጪ ማንም አልነበረም። ዮሴፍ ሰው እንደመሆኑ መጠን ስሜቱን እግዚአብሔር በሰው ጥበብበና ማስተዋልን ተጠቅሞ በገዛ ፈቃዱ ከዝሙት ራቀ። ይህ ነው ዮሴፍን ታላቅ ሰው ያደረገው። (ዘፍ. 39፡11-12)

ዛሬ በዮሴፍ ቦታ ሆነን እንደዚህ ዓይነት የዝሙት ግበዣ ቢቀርብልን የእኛስ ፈቃድ እንዴት ነው? በዝሙት ኃጢአት እንወድቃለን ወይስ? በፈሪሃ እግዚአብሔር በማስተዋለ ከዝሙት ኃጢአት እንርቃለን ወይ? መልሱን ለሕሊናዬና ለሕሊናችሁ ትቸላችኋለሁኝ። ሕዋሳቶቻችን በአግባብ ከጠበቅናቸውና ከተቆጣጠርናቸው የጸጋ ውጤት አላቸው፤ ነገር ግን አለአግባባ ከተጠቅምንባቸው የጸጋው ውበቱ ከውስጣችን ይጠፋና የኃጢአት ባሪያ ያደርገናል።

እግዚአብሔር ሕዋሳቶቻችንን በነጻነት እንድንጠቀምበት ነጻ አድርጐ ፈጥሮናል። በነጻነታችን መጠቀም ወይም አለመጠቀም ምርጫው የእኛ ነው። ልዩነቱ "ውጤቱ ላይ ነው" ይኸውም ሕዋሳቶቻችንን በአግባቡ ከኃጢአት ምንጭ አርቀን፣ ለጽድቅ ሥራ ላይ ከተጠቀምንባቸው ከፈጣያችን ሕይወት እናገኝባቸዋልን። ነገር ግን ሕዋሳቶቻችንን በሥጋችን ፍላጐት የምንጋበዝ ከሆነ በነፍሳችንም ይሁን በሥጋችንም የከፋ ችግር ውስጥ እንገባለን። ስለዚህ ነው ሐዋርያው ቅድስ ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ቃል በመልእክቱ እንዲህ የሚለን "ሥጋውን ለማስደሰት የሚዘራ ከሥጋው ሞትን ያጭዳል፤ መንፈስን ለማስደሰት የሚዘራ ከመንፈስ የዘለዓለም ሕይወትን ያጭዳል" (ገላ 6፡8) ቃሉን በማስተዋል አንብቡት።

የተወደዳችሁ የእግዚአብሔር ቤተሰቦች ሆይ በተሰጡን ሕዋሳቶቻችን ቆም ብለን በማስተዋል እራሳችን "ለምን እነዚህ ሕዋሳቶቻችን በፈጣሪ ተሰጡን?" የሚለውን ጥያቄ መመርመር ያስፈልገናል።

ወደ ገፅ 11 ዞሯል

ይህ ዓምድ በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያንን የጳጳሳት ጉባኤ ጠቅላይ ጽ/ቤት የሴቶችና ቤተሰብ ጉዳይ ክፍል ጋር በትብብር የሚዘጋጅ ነው

**"በመስቀሉ ደም ሰላም አድርጎ በምድር ወይም በሰማያት ያሉትን ሁሉ ለራሱ እንዲያስታርቅ ፈቅዷልና፤" ብሏል። (ቆላ.1፥20)**

# የጸሎት ሐዋርያነት



## ጥቅምት

### ለጋራ ተልዕኮ

ቤተክርስቲያን የኃላፊነት ተምሳሌት በመሆን የካህናት፣ የገዳማውያን እና የምእመናንን ህብረት እና የተልዕኮ ተሳትፎን በሁሉም መንገድ በሲኖዶሳዊ የኗኗር ዘይቤ እንድትቀጥል እንፀልይ።

## October

### FOR A SHARED MISSION

**We pray that the Church continue to sustain in all ways a Synodal lifestyle, as a sign of co-responsibility, promoting the participation, the communion and the mission shared among priests, religious and lay people.**

## የማቅረቢያ ጸሎት

*ቅዱስ አባት ሆይ
ሁሌም ከእኔ ጋር እንደምትሆን አምናለሁ ፤ ልቤን በየቀኑ በቅዱስ ቁርባን ራሱን በሚሰጠን በልጅህ በኢየሱስ ልብ ውስጥ አኖራለሁ። ቅዱስ መንፈስህ እኔን ወዳጅህ እና ሐዋርያህ ያድርገኝ ለአገልግሎትም ዝግጁ እና ቀናኢ ያድርገኝ። ደስታዬን፣ ስቃዬን፣ ተስፋዬን፣ ሥራዬን፣ ሁሉ ነገሬን በዓለም ካሉት የፀሎት ሐዋርያቶች ጋር በአንተ እጅ አኖራለሁ። ከእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ጋር ቀኔን ለቤተክርስቲያን ተልዕኮ አቀርባለሁ! በር.ሊ.ጳ የፀሎት ሐሳብም እፀልያለሁ!*

## ሐዋሳቶቻችን ...

ከገፅ 10 የዞረ

ዛሬ ባለማስተዋላችን ነው እንጂ በተፈጥሮም ይሁን በሰው ሠራሽ ሐዋሳቶቻቸውን ያጡት ስንቶች ናቸው ነገር ግን እኛ በተሰጡን ሐዋሳቶቻችን በማስተዋል ከመጠቀም ፋንታ ለኃጢአት ምንጭ እንጠቀምባቸዋለን። ምክንያቱም ባለማስተዋላችን የተነሳ ነው።

የእግዚአብሔር ቃል ዛሬም እንዲህ ይለናል፡ - "የማያስተውል ሕዝብ ይጠፋል" ትንቢተ ሆሴዕ 4፡14። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም በቃሉ እንዲህ ይለናል "እንግዲህ ሰሚ ጆሮ ያለው ይስማ" (ማር. 4፡22፤ ማቴ. 11፡15) መንፈስ ቅዱስም እንዲህ ይለናል "መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያነ የሚለውን ጆሮ ያለው ይስማ" (ዮሐ. ራዕ 3፡22)።

በተረፈ የሰው ልጅ መጨረሻው ሲያምር ነው መጨረሻችንን እግዚአብሔር ያሳምርልን። እኛም በተሰጡን ሐዋሳቶቻችን ለጽድቅና ለቅድስና ዓላማ በማዋል በተገቢው ሥራ ላይ ማዋል ወይም መጠቀም እንድንችል መንፈስ ቅዱስ ማስተዋልን ወይም የልቦና ጸጋውን በሕይወታችን ዘወትር ያብዞልን። አሜን።

እግዚአብሔር አባታችን ለሀገራችን ኢትዮጵያ እና ለዓለማችንም ሰላሙን ያብዛልን። እኛም ከክርስቶስ ዘንድ የተቀበልነው ሰላምን ለሌሎች ማካፈል እንድንችል የሰላም መሣሪያ ሆነን የክርስቶን ሰላም ወደ ሌሎች ሰዎች ማድረስ እንድንችል እግዚአብሔር በጸጋው ይርዳን። አሜን።

## ምስክሮቼ...

ከገፅ 6 የዞረ

- የተወሳሰቡ አደናጋሪ ቃላቶችን አስወግድ፤ የራስህን ሃሳብና ቃላቶችን ተጠቀም።
- ምስክርነትህን ያለ መንፈስ ቅዱስ መሪነት አታካፍል (1ቆሮ. 3፡1)
- ስትመሰክር ራስህን መንግስተ ሰማይ የገባ ሰው አታስመስለው ።
- ምስክርነትህን አታጋነው፤ ውጤታማ የሚሆነው በእውነተኛነት ላይ የተመረኮዘ ምስክርነት ነው።
- ምስክርነትህን እርጋታ በተሞላበት መንፈስ በማቅረብ አድማጮችህ ኢየሱስ ጌታህ መሆኑን ያውቁ ዘንድ አድርጋቸው።

ስለምስክርነት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሲናገር እንዲህ ያለውን እናስታውሳለን፤ ‹‹ስለዚህ በሰዎች ፊት ለሚመሰክርልኝ ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለው በአባቴ ፊት እመሰክርለታለሁ›› (ማቴ. 10፡32)። በመሆኑም አምላካችንን በመታዘዝ ስለክርስቶስ ስንመሰክር ነፍሳትን የማዳን ኃላፊነታችንን ከመወጣት ባሻገር ለእያንዳንዳችን በአባቱ ፊት እንደሚመሰክርልን እናረጋግጣለን። ስለዚህ እግዚአብሔር አምላክ ወንጌልን የማብሰር ኃላፊነታችንን እንድንወጣ ጸጋውን ያብዛልን።

ምንጭ፡ Terry Barber, How to Share Your Faith With Anyone ( a Practical Manual for Catholic Evangelization)

# የወጣቶች መንፈሳዊ ፌስቲቫል በሆሳዕና ቅዱስ ዮሴፍ ካቶሊክ ካቴድራል

በሆሳዕና ቅዱስ ዮሴፍ ቁምስና ካቶሊክ ካቴድራል ቅጥር ግቢ ውስጥ ከጳጉሜ 3 እስከ 5/2016 ዓ.ም የወጣቶች ፌስቲቫል ተካሄደ። ከተለያዮ ቁምስናዎች የተወከሉ ከሰባት መቶ (700) የሚበልጡ ወጣቶች የተገኙበት ይህ መንፈሳዊ ፌስቲቫል የተለያዩ ፕሮግራሞችን ያቀፈ ሲሆን ክቡር አባ ፊሊጶስ (ከእምድብር ሰበካ) እና ክቡር አባ በቴ (ከመቂ ሰበካ) ስለ ምሥጋና እና ስለትህትና መንፈሳዊ ትምህርት ሰጥተዋል። ክቡር አባ አብነት አበበ (ዘማኅበረ ልኡካን/ላዛሪስት) በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የጳጳሳት ጉባኤ ጠቅላይ ጽ/ቤት የቤተሰብ የምእመናንና የወጣቶች ሐዋርያዊ ሥራዎች አስተባባሪ በፌስቲቫሉ ላይ በመገኘት ‹‹ ክርስቶስ ቤተክርስቲያንን እንደወደዳትና ራሱንም ስለእርሷም ራሱን አሳልፎ እንደሰጠ እናንተም ውደዷት (ኤፌ. 5፡25) በሚል ርእስ ቤተክርስቲያንን ስለመውደድ በዝርዝር አስረድተዋል።

እናታችን ቤተክርስቲያን የቅዱሳንና የኃጢአተኞች ቤት ናት ብትሆንም ልንወዳት ይገባል፣ (ማቴ. 13፡24-30) ይህም ማለት ካቶሊካዊ ማንነታችንን ጠንቅቀን በማወቅና ከሌሎች ኃይማኖቶች ጋር የሚያቀራርቡንን ነገሮች በመለየት በካቶሊካዊት ኃይማኖት ጸንቶ መኖር (2ቆሮ. 11፡3-4)፣ በሰንበት ቀን እና በመንፈሳዊ በዓላት ቀን በቅዳሴ ላይ በመገኘት ሥጋ እና ደሙን መቀበል (ዮሐ. 6፡55-56)፣ መንፈሳዊ አባቶቻችንን ማዳመጥ/መታዘዝና (ዕብ. 13፡17) የቤተክርስቲያንን አንድነት መጠበቅ የሁላችንም ኃላፊነት እንደሆነ መረዳት ለዚህም የአብሮነት ጉዞ አስፈላጊነት (መክብብ 4፡9-12)፣ ከማያምኑ ጋር በማይመች አካሄድ አለመጠመድ (2ቆሮ. 6፡14)፣ ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ ጥሩ አይደለምና (ዘፍ. 2፡18) መሰብሰባችንን ቸል አለማለት (ዕብ. 10፡25) ስለዚህም በኢየሱስ ስም በመሰባሰብ አንድነታችንን ይበልጥ ማጠንከር ቤተክርስቲያንን የመውደዳችን መግለጫ ነውና በመንፈስና በሥጋ የምትመግበንን ቤተክርስቲያን ይበልጥ ልንወዳት ይገባል ብለዋል።

ማክሰኞ ጳጉሜ 5 ቀን 2016ዓ.ም የፌስቲቫሉን የመዝጊያ መስዋእተ ቅዳሴ የመሩትና ወጣቶችን በማበረታታት አምላካችንን ሁሌም ልናመሰግነው ይገባል ያሉት የሰበካው ጳጳስ ብጹዕ አቡነ ስዩም ፍራንሷ ነበሩ። በመጨረሻም የሰበካው እንደራሴና የካቴድራሉ ቆሞስ ክቡር አባ አማኑኤል ዮሴፍ አቡኑንና ካህናትን ተሳታፊ ወጣቶቹንና ምእመናንን በሙሉ አመስግነዋል።

የእግዚአብሔር መንግስት ይስፋ!



# የወጣቶች መንፈሳዊ ፌስቲቫል በወራጉ መድኀኔአለም ቁምስና

ከነሐሴ 17-19/2016 ዓ.ም የወጣቶች ፌስቲቫል በወራጉ መድኃኔአለም ቁምስና ተካሄደ። በኮንሶላታ ልኡካን ማኅበር አባቶች (ክቡር አባ ዮሐንስና አባ ነብያት) የሚመራው ይህ ቁምስና የመንፈስ ቅዱስ ሚሲዮናውያን ሲስተሮች ጋር በመተባበር ባዘጋጁት የወጣቶች ፌስቲቫል ላይ በቁጥር 50 የሚያህሉ ከተለያዩ ቁምስናዎች የተጋበዙ ወጣቶች ተሳትፈዋል። ሲስተር ፔትሮኔላ የወጣቶች ሐዋርያዊ አገልግሎት አስተባባሪ ከሁለቱ ካህናት ጋር በመተባበርና ወጣቶችን በማስተባበር ፌስቲቫሉ የደመቀ እንዲሆን አድርገዋል፤ ይህ ዝግጅት የቅዱስ ቁርባን ስግደት፣ የመቁጠሪያ ጸሎት፣ የንስሐ ጊዜ፣ መስዋዕተ ቅዳሴ፣ ዝማሬ (በግል እና በጋራ) መንፈሳዊ ትምህርት፣ ድራማ፣ ግጥምና የእግር ኳስ ጨዋታን ያካተተ ነበር።

ክቡር አባ አብነት አበበ (ዘማኅበረ ልኡካን/ላዛሪስት) በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የጳጳሳት ጉባኤ ጠቅላይ ጽ/ቤት የቤተሰብ የምእመናንና የወጣቶች ሐዋርያዊ አስተባባሪ በፌስቲቫሉ ላይ በመገኘት ‹‹እንደወደድኳችሁ›› (ዮሐ. 13፡ 34) በሚል ርእስ ስለ እግዚአብሔር ፍቅር አስተምረዋል። ባስተላለፉት ትምህርት እግዚአብሔር እንደወደደን የምናውቀው እንዴት ነው? እኛስ ለፍቅሩ ምላሽ የምንሰጥባቸው መንገዶች የትኞቹ ናቸው የሚሉትን አብራርተዋል።

በመጨረሻም እሁድ ነሐሴ 19 ቀን 2016 ዓ.ም ከቀኑ 3፡00 ሰዓት ላይ ክቡር አባ ታመነ በኢትዮጵያ የኮንሶላታ ማኅበር አለቃ የመንፈሳዊ ፌስቲቫሉ የመደምደሚያ መስዋዕተ ቅዳሴ ቀድሰዋል፤ ክቡር አባ አብነት ደግሞ በእለቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ንባባት ላይ በመመርኮዝ ቃለ ምእዳን አሰምተዋል።

የእግዚአብሔር መንግስት ይስፋ!



ይህ ዓምድ በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያንን የጳጳሳት ጉባኤ ጠቅላይ ጽ/ቤት ከኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያንን የሕፃናት እንክብካቤ እና ጥበቃ ቢሮ ጋር በትብብር የሚዘጋጅ ነው

**"ጠላቶቹ ሳለን ከእግዚአብሔር ጋር በልጁ ሞት ከታረቅን፥ ይልቁንም ከታረቅን በኋላ በሕይወቱ እንድናለን፤ ይህም ብቻ አይደለም፥ ነገር ግን አሁን መታረቁን ባገኘንበት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በእግዚአብሔር ደግሞ እንመካለን፤" ሲል ገልጦታል። (ሮሜ.5፥10-11)**

# የዛፍ እና የድንጋይ ዉህደት

*የምታዩት ዛፍ የበቀለው በድንጋይ ላይ ነው። ይህንን ዛፍ ያየነው በካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የጳጳሳት ጉባኤ ጠ/ጽ/ቤት በፍትህ እና ሰላም የሥራ ክፍል ከሰኔ 25 እስከ ሰኔ 27፣ 2026 ዓ.ም ድረስ የተካሄደውን ትምህርታዊ ዝግጅት ለመካፈል ደብረ ዘይት በሄድንበት ወቅት ነው።*



**በልማዳዊው/ሥጋዊ አእምሮአችን ስናስብ፣ ዛፍ እንዴት በድንጋይ ላይ ሊበቅል ይችላል ልንል እንችላለን። በመንፈሳዊው ዓይናችን ስናየው ግን፣ ምንም ላንገረም እንችላለን፣ ምክንያቱም የሁለቱም ፈጣሪ አንድ ስለሆነ ነው።**

ይህ ዛፍ የሚገኘዉ ደብረዘይት ጋሊሊ ገዳም ውስጥ ነው።

ይህንን ዛፍ በስልኬ ካሜራ በምቀርጽበት ሰዓት፣ ሁለት ሃሳቦች በአእምሮም ይመላለሱ ነበር። በመጀመሪያ እንዲህ ስል አሰብኩ፣ የዛፉን ስር ደግፎ ማሳደግ ያለበት አፈር አይደለም እንዴ? ታዲያ ይህ ከሆነ እና ድንጋይ የዛፍን ሥር አቅፎና ደግፎ መያዝ ከቻለ፣ ለምንድን ነው ታዲያ እኛ ሰዎች ልክ እንደ ዛፉ እና ድንጋዩ ተስማምተን መኖር ያቃተን?

በአሁን ሰዓት በአገራችን በተለያዩ ስፍራዎች ለሚታዩት ግጭቶች ዋናው ምክንያት በሁለት ግለሰቦች እና በሁለት ቡድኖች መካከል ያለው አለመጣጣም እና አለመስማማት ነው ብዬ አስባለሁ። ሌላዉ ምክንያት ደግሞ እንደ ዛፉ እና ድንጋዩ የተሰጠንን የእግዚአብሔር ጸጋ አለማወቃችን ይመስለኛ። እንደ ቅዱስ ፍራንሲስኮስ የመሳሰሉት የጥንት አባቶቻችን የዱር እንስሳትን በማረቅ ፍቅርን አስተምረውናል። ‘ወንድሜ ተኩላ፣ በእየሱስ ክርስቶስ ስም አሁን ወደ እኔ እንድትመጣ እማጸንሃለሁ፣ ምንም የሚያጠራጥር ነገር የለም፣ ና፣ እና በእግዚሐብሔር ስም ሰላምን እንመስርት።’ ከዛም ተኩላው በመታዘዝ ከቅዱስ ፍራንሲስኮስ ጋር መጓዝ ጀመረ።

ከሌሎች ፍጥረታት ጋር ምንም ልዩነት እንደሌለው በመረዳቱ፣ ዛፍ በድንጋይ ላይ መብቀል መቻሉን አልተጠራጠረም፤ ድንጋይ ደግሞ ዛፍ የኔ ዝርያ ስላልሆነ በእኔ ላይ እንዲበቅል አልፈቅድለትም አላለም። የዛፍን እና የድንጋይን እርስ በርስ መደጋገፍ እና መያያዝ ስናስብ፣ የስነ-ሕይወት ሳይንስን ህግ የጣሰ መሆኑን እንረዳለን። ምክንያቱም፣ የስነ-ሕይወት ሳይንስ ሕግ ሕይወት ያለው ነገር ሕይወት ከሌለው ነገር ጋር ዝምድና የለዉም ስለሚል ነው። በመንፈሳዊው ዓለም ግን ሁሉም የእግዚሐብሔር ፍጥረታት ዝምድና አላቸው። (እነሆ፣ እኔ የሥጋ ለባሽ ሁሉ አምላክ እግዚሐብሔር ነኝ፤ በውኑ እኔን የሚያቅተኝ ነገር አለን? ትንቢተ ኤርሚያስ 32፡27)።

የዛፍን እና የድንጋይን አስገራሚ ውህደት ያነሳሁት ያለምክንያት አይደለም። የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የማሕበራዊ ልማት ኮሚሽን የፍትህ እና ሰላም የሥራ ክፍል አገልግሎት ከዛፉ እና ከድንጋዩ ጥምረት ታሪክ ጋር ተዛማጅነት ስላለዉ ነው። የሰላም እና ፍትህ የሥራ ክፍል ሰብዓዊ አገልግሎት ግጭትን ያስወግዳል ብሎ አያምንም። በእርግጥ፣ የሥራ ክፍሉ ሰብዓዊ አገልግሎት በግጭት ሂደት ውስጥ አወንታዊ እና አሉታዊ ተጽዕኖ አለዉ ብሎ ያምናል። ሰብዓዊ አገልግሎቱ በጥንቃቄ ካልተያዘ፣ በተጠቃሚዎች መረጣ፣ በግዢ አቅርቦት ላይ፣ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ፣ እንዲሁም ተፈናቃዮችን መልሶ በማቋቋም ላይ ተጽዕኖ በማሳደር ግጭቶችን ሊያባብስ ይችላል። በተመሳሳይ ሁኔታ፣ ሰብዓዊ ዕርዳታ ውጥረቶችን በመቀነስ እና በሀብት ላይ የሚደረግን ፉክክር በመከላከል አዎንታዊ ተጽዕኖ ሊያሳድር ይችላል።

በግጭት ዉስጥ ጥምረትን ለመፍጠር፣ የፍትህ እና ሰላም የሥራ ክፍል አጠቃላይ ግጭቶች ስለሚፈጠሩባቸው ሁኔታዎች እና ‘Do No Harm’ በሚለው መርህ መሥራት በሚቻልበት መንገድ ዙሪያ ለልማት ሠራተኞች የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርታዊ ዝግጅት አካሂዷል። የትምህርታዊ ዝግጅቱ ዓላማም፣ የሰላም ግንባታ ሂደቱን ከእያንዳንዱ ፕሮግራም እና ፕሮጄክት ጋር ማዋሃድን ያለመ ነው። ታዲያ የዛፉ እና የድንጋዩ ውህደት ምሳሌ የሚመጣዉ እዚህ ጋር ነው። ግጭት የሚፈጠረዉ ሁለት ግለሰቦች፣ ሁለት ማሕበረሰቦች በልማት ተጠቃሚነት ምክንያት ፍላጎታችን እና የሕይወት ግባችን ከሚሠራው የልማት ሥራ ጋር አይጣጣምም፣ አይስማማም፣ ወይም ደግሞ ተጻራሪ ነው ብለው ሲያስቡ ወይም ሲያምኑ ነው።

የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የልማት ኮሚሽን የፍትህ እና ሰላም የሥራ ክፍል ግጭትን እና ግንኙነትን አንድ ላይ ለመቃኘት(ግጭትን ወደ ግንኙነት መስመር ለመቀየር) መከተል ያለበት አሠራር ምንድን ነው?

የፍትህ እና ሰላም የሥራ ክፍል በዋናነት የሚሰራዉ አለመግባባቶችን እና ግጭቶችን ለመፍታት እና ሰላምን ለመገንባት በልማት ሠራተኞች እና ተጠቃሚዎች ዘንድ ገጭት ከመፈጠሩ በፊት አስቀድሞ የመረዳትን አጠቃላይ ሁኔታ በማስጨበጥ ላይ ያተኮረ ነው። ግጭት ከመፈጠሩ በፊት አስቀድሞ የማሸተት ክህሎት የልማት ኮሚሽኑ የሚከተሉትን ሥራዎች እንዲሰራ ያስችሉታል፡

1. የልማት ሥራዎችን የሚሰራባቸውን አካባቢዎች አጠቃላይ ሁኔታ ለመረዳት ያስችለዋል።
2. በልማት ሥራዉ እና በሥራዉ ከባቢ መካከል የሚደረጉ ግብይቶችን ለመረዳት ያስችለዋል።
3. ከላይ የተገለጹትን በመረዳት ሊደርሱ የሚችሉ አሉታዊ ተጽዕኖዎችን ለመቀነስ እና አዎንታዊ ተጽዕኖዎችን ለመጨመር ያስችሉታል።

በእያንዳንዱ ፕሮግራም እና ፕሮጄክት ላይ ሊደርሱ የሚችሉ ግጭቶችን አስቀድሞ የመረዳት እና የማሸተት የአሠራር ዘዴን ቢከተል፣ የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የልማት ኮሚሽን የሚከተሉትን ማድረግ ያስችለዋል፡

4. በልማት ፈጻሚዎች እና ተጠቃሚዎች መካከል ሊኖር የሚችለውን ውጥረት ለመለየት ያስችለዋል።
5. በሚሰራበት አካባቢ ሳይታሰቡ ውጥረትን ሊቀሰቅሱ ወይም በሰዎች መካከል ክፍፍልን ሊፈጥሩ የሚችሉ ድርጊቶችን ወይም ውሳኔዎችን ለማስወገድ ያስችለዋል።
6. በተከሰቱ ወይም ወደፊት ሊከሰቱ በሚችሉ ግጭቶች ምክንያት የማሕበረሰቡን ተጋላጭነት በመገመት እና ማሕበረሰቡ በመጪው ጊዜ በሚፈጠረው የሰላም ግንባታ ላይ ስላለው ዋነኛ ፍላጎት እና ሚና በመረዳት ምላሽ ለመስጠት ያስችለዋል።
7. በተከፋፈሉ የማሕበረሰብ ክፍሎች ወይም ባለድርሻ አካላት መካከል ማሕበራዊ ትስስርን ማጠናከር እንደሚቻል በመረዳት፣ ግጭትን በጋራ የሚከላከል እና በቀላሉ የማይከፋፈል ማሕበረሰብ ለመፍጠር ያስችለዋል።

በመጨረሻም፣ ግጭት በአንድ ተቋም ውስጥ በእያንዳንዱ የግንኙነት እርከን የሚፈጠር በመሆኑ፣ የሰላም ግንባታ ሂደት በተቋሙ የተለያዩ አደረጃጀቶች ውስጥ የሚገኙ የሥራ መሪዎችን፣ ከታችኛው የአደረጃጀት መዋቅር አንስቶ እስከ ላይኛው መዋቅር ድረስ የሚገኙ ሠራተኞችን፣ እንዲሁም ደግሞ የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን፣ ማለትም ለጋሾችን፣ የማሕበረሰብ ክፍሎችን፣ የአካባቢ አስተዳደሮችን የመሳሰሉትን ሁሉ ትብብር ይጠይቃል።

በ ጥበበ ኃይለጊዮርጊስ

---

## የጌታችን ኢየሱስ...

ከገፅ 7 የዞረ

ለዚህም ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ “ከእንግዲህስ ወዲያ ለኃጢአት እንዳንገዛ የኃጢአት ሥጋ ይሻር ዘንድ አሮጌው ሰዎችን /ሰውነታችን/ ከእርሱ ጋር እንደተሰቀለ እናውቃለን።” ያለው (ሮሜ.6፥6)። ዳግመኛም በቆሮንቶስ መልእክቱ ላይ “ስለዚህ ማንም ቢሆን በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፏል፤ እነሆ ሁሉም አዲስ ሆኗል፤” ብሏል። (2ኛ ቆሮ.5፥17)። ቅዱስ ጳውሎስ እንደተናገረው፡ - ጌታችን እኛን በቤዛነቱ አዲስ አድርጎናል፥ አዲስ ሕግ ወንጌልንም ሰጥቶናል፥ አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር መንግሥተ ሰማያትንም አዘጋጅቶልናል። (ማር.1፥15፣ 2ኛ ጴጥ.3፥13፣ ራእ.21፥1)።

### የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ሁላችንም አንድ አድርጎናል

በኃጢአት ምክንያት ከእግዚአብሔር ጋር ተጣልተን እንኖር ነበር። ይሁን እንጂ እኛ በበደልን እርሱ ክሶ በቤዛነቱ መልሶ ታርቆናል። ይህንንም ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ “ጠላቶቹ ሳለን ከእግዚአብሔር ጋር በልጁ ሞት ከታረቅን፥ ይልቁንም ከታረቅን በኋላ በሕይወቱ እንድናለን፤ ይህም ብቻ አይደለም፥ ነገር ግን አሁን መታረቁን ባገኘንበት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በእግዚአብሔር ደግሞ እንመካለን፤” ሲል ገልጦታል። (ሮሜ.5፥10-11)። በተጨማሪም “በመስቀሉ ደም ሰላም አድርጎ በምድር ወይም በሰማያት ያሉትን ሁሉ ለራሱ እንዲያስታርቅ ፈቅዷልና፤” ብሏል። (ቆላ.1፥20)። በኤፌሶን መልእክቱም “ሁለቱን ያዋሐደ በአዋጅ የተነገሩትንም የትእዛዛት ሕግ ሽሮ በመካከል ያለውን የጥል ግድግዳ በሥጋው ያፈረሰ፤ ይህም ከሁለታቸው አንድ አዲስን ሰው በራሱ ይፈጥር ዘንድ ሰላምንም ያደርግ ዘንድ፥ ጥልንም በመስቀሉ ገድሎ በእርሱ ሁለታቸውን በአንድ አካል ከእግዚአብሔር /ከራሱ/ ጋር ያስታርቅ ዘንድ ነው፤” ብሏል። (ኤፌ.2፥14-16፣ 2ኛ ቆሮ. 5፥17)። በመሆኑም ይህ ሁሉ ነገር የተገኘበት መስቀል፡-

### የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል ኃይላችን ሆኖናል

“የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት፥ ለእኛ ለምንድን ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነውና፤” (1ኛ ቆሮ.1፥18) ተብሎ እንደተነገረ፥ የእግዚአብሔር ኃይሉ የተገለጠበት ኃይለ እግዚአብሔር ክርስቶስ የማዳን ሥራውን የፈጸመው በመልዕልተ መስቀል ተሰቅሎ ነው። በመሆኑም የጌታችን ቅዱስ ሥጋው የተፈተተበትና ክቡር ደሙም የፈሰሰበት መስቀል ስለ ክርስቶስ የከበረ ነው።

**ይህ ዓምድ በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የጳጳሳት ጉባኤ ጠቅላይ ጽ/ቤት ከኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን የሕፃናት እንክብካቤ እና ጥበቃ ቢሮ ጋር በትብብር የሚዘጋጅ ነው**

**የታተማችሁበትን ቅዱሱን የእግዚአብሔር መንፈስ አታሳዝኑ” (ኤፌ 4፡30)**

LINK
No. 269 September 2024 P. O. Box 2454 Tel. (0111) 55 03 00 Addis Ababa

You are most welcome to
Subscribe and Advertise on LINK

# The Episcopal consecration of the new Bishop for the Vicariate of Soddo, was held on 15th September 2024

***Bishop Dejene Hidoto was ordained in a solemn ceremony at the Holy Trinity Catholic Cathedral in Soddo, Ethiopia.***



The celebration began with a warm reception as Bishop-elect Dejene arrived from his preparation at the Tikur Weha retreat center near Hawassa, Ethiopia. In attendance were the City Mayor, esteemed Bishops, local government officials, and guests from across the country. Despite heavy rain on the evening of 14th September, the youth and Police band joyfully welcomed Bishop-elect Dejene and the guests, creating a memorable atmosphere. The local community honored their esteemed visitors with a traditional welcoming ceremony as a gesture of respect.

His Eminence Cardinal Abune Berhaneyesus, President of the Catholic Bishops' Conference of Ethiopia, presided over the Holy Mass and consecration ceremony for the new Bishop on 15th September. All bishops were present, except for Bishop Tsegaye, former Bishop of Soddo, and Bishop Tesfasellasie of Adigrat.

More than 250 priests, representatives from other religions, and thousands of faithful gathered to witness this momentous occasion.

Monsignor Massimo Catterin, Secretary to the Nunciature, read the official letter from Pope Francis, confirming the episcopal appointment and formal transfer of leadership for the Vicariate.

In his homily, Cardinal Abune Berhaneyesus extended a heartfelt welcome to the newly consecrated Bishop, calling on everyone to support him through prayer and dedicated service. Addressing the Bishop-elect directly, he said, "Be a faithful guardian of the Church, serve the Church wholeheartedly, always remembering the Good Shepherd. Love the poor and listen to the faithful."

Solidarity messages were shared by former Bishop Tsegaye, who could not attend due to illness, as well as Bishop Seyoum who was service the Vicariate as administrator. Government officials, the international Capuchin Friary Provincial, and representatives of the faithful also voiced their support.

At the close of the ceremony, Bishop-elect Dejene, citing his motto, "Do whatever he tells you" (John 2:5), and emphasized that his ministry will be guided by the words of the Holy Mary from John 2:5. He reflected on how Mary's apparitions at Lourdes constantly inspire him to remain a faithful servant of the Church. Furthermore, he articulated his commitment to serving the Church, especially in the context of Liturgical celebrations in Ethiopia, with a particular focus on the Latin rite. Expressing heartfelt gratitude for the presence of the Bishops, distinguished guests, and fellow Catholics, Bishop Dejene called for their collective prayers and support.

# Bishop Milkiyas, the newly appointed Bishop of the Vicariate of Nekemte, has been anointed

**In a momentous continuation of blessings marking the Ethiopian New Year, the Ethiopian Catholic Church celebrated the episcopal consecration of Bishop Milkiyas, who has been appointed as the Bishop for the Vicariate of Nekemte.**



The ordination occurred on September 22, 2024, at the Kidane Mihret Catholic Cathedral in Nekemte. The ceremony was started by a warm welcome ceremony then followed by a Holy Mass and consecration presided over by His Eminence Cardinal Abune Berhaneyesus, President of the Catholic Bishops' Conference of Ethiopia.

Among the attendees was the former Bishop Varghese Thottamkara, C.M., the current Bishop of Balasore, India, alongside various bishops, priests, special invitees, religious groups, families, and devoted faithful from across the country.

In his homily, the Cardinal emphasized the sacred duty of passing down the title of priesthood from generation to generation, a tradition empowered by the Holy Spirit received from Jesus Christ. After conveying his heartfelt wishes, His Eminence entrusted Abune Milkyas with the responsibility of leading this new ministry appointed by God, urging all Catholics to support their new shepherd with patience and prayer.

In 2024, Pope Francis made a historic decision by appointing three new bishops for the Ethiopian Catholic Church, fulfilling the long-held prayers and aspirations of the faithful in three dioceses. These significant appointments include Bishop Lukas for the Eparchy of Emdibir, Bishop Dejene for the Vicariate of Sodo, and Bishop Milkias for the Vicariate of Nekemte. This long-awaited development marks a monumental milestone for the Ethiopian Catholic Church, which had been earnestly seeking local leadership for its spiritual and pastoral mission. The events were attended by a significant number of faithful from across Ethiopia and neighboring countries, including bishops, priests, religious sisters, and laypeople from Eritrea, AMECEA (Association of Member Episcopal Conferences in Eastern Africa), and SECAM (Symposium of Episcopal Conferences of Africa and Madagascar). This gathering reflected the broader unity of the African Catholic Church and its role in global Catholicism.

The consecration ceremonies were not only deeply spiritual but also highly communal, celebrated with overwhelming joy and participation from all sectors of society, including local communities, youth groups, government officials, and representatives from various religious organizations. This large and diverse turnout demonstrated the strong bond between the Church and the Ethiopian people, as well as the important role the Church plays in both the spiritual and social life of the nation. The presence of ecumenical and government representatives also showcased the Catholic Church's commitment to interfaith cooperation and dialogue, a key focus that the newly appointed bishops are expected to further develop and strengthen.

In light of Ethiopia's current conflicts, social unrest, and growing humanitarian needs, the Catholic Church is seen as a pivotal player in the country's ongoing efforts toward peacebuilding and reconciliation. The consecration of these three bishops comes at a time when the Church is called to collaborate more closely with the government and other religious bodies to address these pressing challenges. The promotion of peace, dialogue, and mutual understanding between communities will be a central mission for the new bishops as they work to heal divisions and foster a spirit of cooperation and unity.

One of the most memorable aspects of the celebrations was the incorporation of Ethiopian cultural traditions into the liturgy, reflecting the inculturation of the Catholic faith. Traditional music, attire, and rituals were harmoniously integrated into the ceremonies, enriching the spiritual atmosphere while showcasing the Church's respect for Ethiopia's diverse cultural heritage. This blending of Catholic and local customs symbolized the Church's commitment to mutual coexistence and solidarity among different ethnic and religious communities in Ethiopia. The new bishops, with their deep understanding of local culture, will be well-positioned to continue this effort, ensuring that the Church remains relevant and rooted in the communities it serves.

The appointment and consecration of Bishop Lukas, Bishop Dejene, and Bishop Milkias are seen as pivotal moments for the Ethiopian Catholic Church. These new leaders are expected to play a critical role in advancing the Church's mission of evangelization, social service, and interfaith dialogue, while also serving as beacons of hope and unity for their respective dioceses. As they begin their pastoral duties, the faithful eagerly look to these shepherds to guide their communities in faith, nurture spiritual growth, and strengthen the bonds between the Church and the broader society. This landmark event represents not only a new chapter for the dioceses but also a vital step forward for the continued development of the Catholic Church in Ethiopia.

For if you forgive men their trespasses, your heavenly Father will also forgive you: But if ye forgive not men their. trespasses, neither will your Father forgive your trespasses. (Matthew 6:14-15)

# Pope Francis Returns to the Holy See After Concluding 45th Apostolic Journey in Asia and Oceania

Pope Francis embarked on his 45th Apostolic Journey abroad, departing from Rome's Fiumicino Airport for a 12-day visit to Indonesia, Papua New Guinea, Timor-Leste, and Singapore. This journey marks the longest of his papacy, highlighting his commitment to fostering peace, dialogue, and interreligious cooperation. Upon landing in Jakarta after more than 13 hours, the Pope was welcomed by Indonesia's diverse population, where Catholics represent only a small percentage. His visit emphasizes Indonesia's commitment to peaceful cohabitation and diversity, as rooted in the country's founding principles, with enthusiastic support from people of various faiths.

During his stay in Indonesia, Pope Francis engaged in several key activities, including an interreligious meeting at Jakarta's Istiqlal Mosque, where he underscored the importance of friendship and mutual respect across religious traditions. Accompanied by the Grand Imam, Dr. Nasaruddin Umar, the Pope highlighted the significance of nurturing unity amidst diversity. His meeting with young people further conveyed the message that differences can lead to dialogue rather than conflict, reinforcing the value of understanding and harmony. His visit also included a celebration of Mass, where he encouraged the faithful to dream of fraternity and continue fostering kindness in their communities.

The next leg of the journey took Pope Francis to Papua New Guinea, where he praised the country's cultural and tribal diversity, while also appealing for an end to violence and division. Addressing civil authorities, he emphasized the need for dialogue and cooperation to improve health, education, and employment opportunities for all. During his visit to Port Moresby, the Pope met with street children and those with disabilities, offering them words of encouragement and reminding them of their inherent value in God's eyes. He also encouraged the local clergy to continue their mission with hope and courage, despite challenges.

In Timor-Leste, Pope Francis met with enthusiastic crowds and focused his messages on the integration of faith into the culture of the people. Addressing large gatherings, including one with nearly half of the country's population, he celebrated the vibrancy and youthfulness of the nation. He underscored the importance of welcoming and caring for children as a symbol of the nation's future. The Pope's homily during a Mass reflected his deep appreciation for the Timorese people's faith and resilience, as he encouraged them to make space for the younger generation and prioritize their well-being.

The final stop on the journey was Singapore, where Pope Francis was welcomed warmly. He recognized Singapore as a model of progress, inclusivity, and environmental stewardship. Addressing the nation's authorities, he called for continued efforts toward social justice and sustainability, praising the city-state's initiatives in these areas. During his time in Singapore, the Pope has met with religious leaders and young people, emphasizing the importance of unity and dialogue among different faiths. His interreligious message reiterated that all religions are paths to God, urging the youth to foster understanding and unity in their communities.





Pope Francis concluded his Apostolic Journey with a Mass at Singapore's National Stadium, where he centered his homily on love as the core of the Gospel. This message encapsulated the spirit of his 12-day journey through Asia and Oceania. As he boarded the papal plane to return to Rome, the Pope's mission of peace, dialogue, and care for creation was evident throughout his travels. Upon his return, he stopped at the Basilica of St. Mary Major in Rome, offering thanks to the Blessed Virgin Mary for her protection during this historic visit.

# Retreat is an integral part of Christian life

It is a definite time spent away from one's normal life for the purpose of reconnecting, usually in prayer, with God. For every Consecrated Person who is actively involved in God's work is encouraged to take out time to be with the God of the work. The practice of leaving one's everyday life to connect on a deeper level with God, in a quiet place is nearly as old as Christianity itself

Therefore, from the 14th – 21st of September, 2024, Seventeen (17) Consecrated Women working in Ethiopia, of nine different nationalities from various Congregations met at the Consolata Retreat Centre, Modjo. The goal was to make a "Contemplative Retreat" which was organized by Conference of Major Religious Superiors (CMRS) yearly for the Consecrated Persons in Ethiopia. The Retreat Director, Fr. Anton Altnoeder S.J has been coming in the last six years to guide such a retreat in Ethiopia. Contemplative retreat is a long periods of silence and solitude. This type of retreat differs from Guided , Directed or Preached retreats. In directed retreats, individuals meet with a spiritual director for prayer and reflection while Guided retreats follow the same format as directed retreat, but usually include an experience of individual or communal faithsharing and processing at the end of the day. Preached retreats are led and preached by priests, Religious or Lay faithful. In contemplative retreat, emphasis on awareness of God present in all his creatures (environment) and becoming aware of what goes on within.

This kind of prayer practice is meant to guide retreatants to grow from self – Centeredness to God-Centeredness and not only during the retreat but eventually in all aspects of our life. In this retreat, at least a quarter of a day i.e. six hours is spent in group meditation together in absolute silence. Most of the participants had no previous experience in this way of prayer, therefore, the meditation periods were a bit stressful at the beginning for some but gradually got used to it. Step by step we were guided to be aware of the environment with the use of all our senses and to be attentive to the outside world into ourselves, following our breathing process, meditating on the power and energy that flows to the hands and palms for about three days, and eventually to pray with the name of Jesus.

Being on this journey together in a group was a big support. The faithfully observed silence and presence of all for all prayer sessions was experienced as a help, especially when one experiences a lack of energy and discouragement. In the end, all were glad and grateful to have lived through the experience. With God's grace and faithful prayer practice, we will grow into greater awareness of God's presence in our life.

Only the Consecrated Women took part this year, it is hoped that our Male counterpart will be available to take part in the subsequent ones to come. The participants are grateful to Fr. Anton and CMRS for this opportunity.





This page is sponsored by CRS

"According to your faith [your trust and confidence in My power and My ability to heal] it will be done to you." (matthew 9 29)

# Newly Appointed Three Bishops for the Ethiopian Catholic Church



**Bishop Dejene**
Apostolic Vicariate of Soddo

**Bishop Milkiyas**
Apostolic Vicariate of Nekemt

**Bishop Lukas**
Eparchy of Emdibir

This page is sponsored by CAFOD/SCIAF/TROCAIRE

" God is faithful, who has called you into fellowship with his Son, Jesus Christ our Lord.". (1 Cor. 1:9)

# LINK

# የጥሪ ማዕድ

## የሕክምና ተልዕኮ እህቶች ማኅበር
## Medical Mission Sisters

*Called to be a healing presence at the heart of a wounded world*

**“ብርሃናችሁ በዓለም ሁሉ ይብራ”** ማቴ. 5: 16

“let your light shine” Mt. 5 - 16



ማህበራችን እ.ኤ.አ በ1925 በሲስተር አና ደንግል (ዶር) Sister Anna Dengel (Dr.) በአሜሪካ ተመሠረተ

**የማህበራችን ዋነኛው ዓላማ -** የክርስቶስን የማዳን ሥራ አገልግሎት በሕክምናና በተለያዩ የአገልግሎት ዘርፎች ቀጣይነት እንዲኖረው ማድረግ።

**መስፈርታችን -**

- በቅድሚያ ሕይወቷን ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር አገልግሎትና ለድሆች መስጠት የምትፈልግ
- ለጸሎትና ለእግዚአብሔር ትልቅ ስፍራ ያላት
- በዓለም አቀፍ ማኅበር መኖርና ማገልገል የምትፈልግ
- የትምህርት ደረጃ 10+2 እና ከዚያም በላይ

ቦሌ ጌስት ሃውስ አካባቢ
ቤት ቁጥር - 68
አድራሻችን አዲስ አበባ / ቂርቆስ - ወርዳ 01

የስልክ ቁጥር
0911055968
0911400139
0911106561
0923241466

ፖ.ሣ. ቁጥር 2891

አድራሻችን ወልቂጤ ጉራጌ
ስልክ ቁጥር 011 3 30 52 37
ፖ.ሣ. ቁጥር ሲስተር ንግሥት ብሩ
11

## የኮንሰላታ ማርያም ልውካን እህቶች እና አባቶች ገዳም

“የኮንሰላታ የአጽናኝቷ ማርያም ልውካን እህቶች እና አባቶች ገዳም ዓለም አቀፍ ተልዕኮ ያለው ሲሆን የገዳማችን ልዩ ምልክት እግዚአብሔር ኢየሱስን አጽናኝ አድርጎ ለዓለም እንደሰጠ እኛም ለዓለም ሁሉ የምሥራቹን ቃል ማብሰር ነው።”


**“.... ሕዝቤን አጽናኑ አጽናኑ” (ኢሳ. 40 :1)**

እኛ የአጽናኝቷ ማርያም ልውካን እህቶች እና አባቶች በብፁዕ ዮሴፍ አላማኖ አማካኝነት ቶሪኖ በሚባል በጣሊያን ከተማ ገዳማችን ተመሰረተ።

የተጠራነውም በፍቅር እንድንኖርና በተጠራንበት የፍቅር ሕይወት የእግዚአብሔርን ቃል ላልሰሙት ለማብሰር ነው። ይህንንም የምናደርገው በሕብረት በመኖር፣ ዛሬ በምንገኝባቸው አገሮች፣ በአፍሪቃ፣ በእስያ፣ በአውሮፓ፣ በሰሜንና በደቡብ አሜሪካ ከማህበረሰቡ ጋር በመኖር የተለያየ አገልግሎት በመስጠት ላይ እንገኛለን።

**የገዳማችንን መንፈስ ለመከተልም ሆነ የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ፍቅር እና መፅናናት ላልደረሳቸው ለማድረስ ለምትሹ እህቶች/ ወንድሞች ሁሉ -** የገዳማችን መጠይቅ እንደሚከተለው ነው

1. በቅድሚያ ራሷን/ራሱን ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር አገልግሎት መስጠት የምትፈልግ/ የሚፈልግ
2. የእግዚአብሔርን ቃል ላልደረሳቸው ማብሰርና የተልኮ ሕይወት ለመኖር ሙሉ ፍላጎት ያላት/ ያለው
3. 10+3 ወይም ዲፕሎማ 12+3 Degree (ዲግሪ) ከዛም በላይ በማንኛውም ዘርፍ የትምህርት ማስረጃ ያላት/ ያለው
4. ለአባቶች 12ኛ ክፍል ይቀበላሉ



Our Lady of Consolata
Pray for Us

**“ታላቅነቴን በሕዝቦች መካከል ያውጃሉ” (ኢሳ. 66 :18)**

ስልክ
**0912-14-26-37**
**011-3-21-01-47 / 48**

የፖ.ሳ ቁጥር
**145069 / 22748**

አድራሻ
**ኮንሰላታ ሲስተሮች/ አባቶች አዲስ አበባ መካኒሳ ከመካነየሱስ ሴሚናሪ ፊት ለፊት**

## በአዲስ አበባ ካቶሊክ ሃገረስብከት ሴቶች ዕድገት ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ማዕከል

(ካሀሴዕማ/ቴ/ሙ/ት/ስ) አ.አ.

**Catholic Archdiocese Women's Promotion Technical and Vocational Education & Training Center**

(CAWPC / TVET) A. A

**“Come and see us. You will be most welcome! WE ARE WAITING FOR YOU!”**

በዝቅተኛ የኢኮኖሚ ደረጃ ላይ የሚገኙና የቀለም ትምህርታቸውን በተለያዩ ምክንያቶች አቋርጠው የሙያ ስልጠና ፍላጎት ያላቸውን ወጣቶች ለማገዝ በአነስተኛ ክፍያ የስልጠና አገልግሎት በማግኘት ለሥራ ብቁ የሚያደርጉና ለገቢ ማስገኛ እንቅስቃሴ የሚያዘጋጁ የሙያ ስልጠናዎችን በመስጠት ላይ እንገኛለን።

**በአጫጭር ስልጠና**
**(Short training)**
በደረጃ አንድና በደረጃ ሁለት
Level (1) one and Level (2) two

**የሚሰጡ ስልጠናዎች**

1. ልብስ ቅድና ስፌት
2. ህትመትና ማቅለም
3. የተሻሻለ የሽመና ሥራ
4. ጥልፍ በእጅና በስፌት መኪና
5. ሹራብ በእጅና በማሽን
6. ምግብ ዝግጅትና መስተንግዶ

ሀ - ከ 3-6 ወራት አጭር ኮርስና
ለ - ለ 10 ወራት በመረጡት ሙያ ሰልጥነው እራስዎን ለሥራ ያዘጋጁ።

**በማዕከላችን የስልጠና አገልግሎቱ ቀጣይነት በጥራት የሚያመርታቸውን የዕደጥበብ ምርቶች በተመጣጣኝ ዋጋ በመግዛት ተጠቃሚ እንዲሆኑ እንጋብዛለን።**

**አድራሻችን**
አራዳ ክ/ከ ፒያሳ
ካቶሊክ ካቴደራል ት/ቤት
ቅጥር ግቢ ውስጥ

**ስልክ ቁጥር**
011 111 4786 / 011 157 5927

**E-mail**
cawpc@ethionet.et

**ስለ“ፍቅርና ሰላም ጋዜጣ” አስተያየት ካለዎት በስልክ ቁ. (0111) 55 03 00 በመደወል ለፍቅርና ሰላም ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ያካፍሉን!**




## በላይ ተክሉ ብስኩት ቤት
*Belay Teklu Pastry*

- ለሰርግ
- ለልደት
- ለተለያዩ ግብዣዎች

የሚሆኑ ኬኮችን አዘጋጅቶ ይጠብቃችኋል





አድራሻችን
ልደታ መልሶ ማልማት ፓርክ ፊት ለፊት
አዲስ አበባ

የመ.ሣ.ቁ
1928

0911203273
0911208810
0913303412

## የካቶሊክ ቤተክርስቲያን መንፈሳዊ መጻሕፍት መደብር
**Catholic Church Book Shop**

ፒያሳ - ካቴድራል ት/ቤት ገባ ብሎ በስተቀኝ

ፖ. ሣ. ቁ. 2454 አዲስ አበባ

ስልክ:
(0111) 55 03 00




**ወንጌልን በጋራ እንስበክ**

**ሌሎች ቢያነቡዋቸው ትምህርት ያገኙባቸዋል ብለው የሚያምኑባቸውን መጣጥፎች እና የወንጌል አስትምህሮዎች ይላኩልን**

ፖ. ሣ. ቁ. 2454 አዲስ አበባ    ስልክ - (0111) 55 03 00    ፋክስ (0111) 55 31 13    E-Mail - scpr@eccsdco.org

Published Monthly by ECS, Social Communications & PR Department    Printed at ECS